# የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር ስትራቴጂክ ዕቅድ [2010–2014]

የፋይናንስ የህግ ማዕቀፍ

ፕሮግራም በጀት

ፊስካል ፖሊሲ

ኤሌክትሮኒክ ግዥ

ኤሌክትሮኒክ ክፍያ

ዘመናዊ ሂሳብ አያያዝና ሪፖርት

ዘመናዊ ንብረት አስተዳደር

የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት

የፋይናንስ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ

የአቅም ግንባታ

ፋይናንስ ግልፅነትና ተጠቂነት

ማህበራዊ ተጠያቂት

መጋቢት/2010 ዓ.ም

ገ/ኢ/ት/ሚ/ር

# የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር ስትራቴጂክ ዕቅድ [2010-2014]




መጋቢት/2010 ዓ.ም
ገ/ኢ/ት/ሚ/ር

# ማውጫ


1. መግቢያ ........ 1

1.1 የትኩረት አቅጣጫዎች ........ 1

1.1.1 ራዕይ (Vision) ........ 1

ሀ. የሚኒስቴሩ ራዕይ ........ 1

ለ. የስትራቴጂው ራዕይ ........ 1

1.1.2 ተልዕኮ (Mission) ........ 2

ሀ. የሚኒስቴሩ ተልዕኮ ........ 2

ለ. የስትራቴጂው ተልዕኮ ........ 2

1.2 የስትራቴጂው ዓላማ ........ 2

1.2.1. የስትራቴጂው ዋና ዓላማ ........ 2

1.2.2. የስትራቴጂው ዝርዝር ዓላማዎች ........ 2

1.3 የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር ትርጓሜ ........ 3

1.4 የስትራቴጂው ወሰን ........ 3

2. የመንግሥት ፋይናንስ አስተዳደር የማሻሻያ ስራዎች አጀማመር ........ 3

3. የመንግሥት ፋይናንስ አስተዳደር ማሻሻያ ስራዎችና የተገኙ ውጤቶች ........ 5

3.1. የሕግ ማዕቀፍ ........ 5

3.2. የመካከለኛ ዘመን ፊሲካል ማዕቀፍ እና የፕሮግራም በጀት ........ 5

3.2.1. የመንግሥት ገቢ እና ወጪ ዕቅድ ማሻሻያ ........ 5

3.2.2. የመንግስት በጀት ዝግጅትና አስተዳደር ........ 6

3.3. የመንግሥት ጥሬ ገንዘብ፣ ክፍያ እና ብድር አስተዳደር ሥርዓት ........ 6

3.3.1. የመንግሥት ጥሬ ገንዘብ አስተዳደር እና ክፍያ ሥርዓት ........ 6

3.3.2. የመንግሥት ብድር አስተዳደር ሥርዓት ........ 7

3.4. የመንግስት የሂሳብ አያያዝና ሪፖርት አቀራረብ ሥርዓት ........ 7

3.5. የመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ........ 8

3.6. የውስጥ ኦዲት ........ 8

3.7. ዘመናዊ የመረጃ ስርዓት አጠቃቀም ........ 8

3.8. የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት ........ 9

4. ልማታዊ መንግስት እና የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር ........ 9

4.1. የመንግሥት ገቢ ማሻሻያ ........ 10

4.2. የመንግሥት ወጪ አመዳደብና አስተዳደር ........ 12

4.3. የልማትና የድህነት ቅነሳ ፖሊሲና እስትራቴጂ ........ 12

4.4. ድህነት ተኮር ወጪዎች ..... 13
4.5. የመንግሥት ወጪን ውጤታማ ማድረግ ..... 14
4.6. ያልተማከለ የፋይናንስ አስተዳደር (DEEPEN FISCAL DECENTRALIZTION) ..... 14

5. ውስጣዊ እና ውጫዊ ሁኔታዎች ትንተና ..... 15
5.1. ውስጣዊ ሁኔታ ..... 15
5.2. ውጫዊ ሁኔታ ዳሰሳ ..... 17
5.2.1. መልካም አጋጣሚዎች ..... 17
5.2.2. ሥጋቶች ..... 18
5.2.3. አስቻይና ፈታኝ ሁኔታዎች ..... 18

6. የስትራቴጂው የትኩረት መስኮችና ግቦች ..... 19

7. የስትራቴጅው አመራርና ተቋማዊ አደረጃጀት ..... 26
7.1. ስትራቴጅውን ለመምራት ዋና ዋና መሰረታዊ ጉዳዮች (MAIN PRINCIPLES) ..... 26
7.2. ተቋማዊ አደረጃጀት፣ ክትትልና ግምገማ ..... 26
7.3. ስትራቴጂውን ለማስፈጸም የሚያስፈልግ በጀት ..... 29
7.4. የስትራቴጂክ ዕቅድ ትግበራ የድርጊት መርሐ ግብር (Result Framework) ..... 30

# 1. መግቢያ

መንግስት በየዓመቱ የሚመድበው በጀት የአገሪቱን የዕድገት ዓላማ ለማሳካትና ድህነትን ለመቀነስ ብሎም ለማስወገድ ሚናው የጐላ የሚሆነው የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር በስትራቴጅክ ዕቅድ ሲመራ ነው፡፡ መንግስት አገራዊ ኢኮኖሚውን ለማሳደግና የሕዝቡን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል የረጅም፣የመካከለኛና የአጭር ጊዜ ፕሮግራሞች በማዘጋጀትና እና ፕሮጀክቶች በማቀድ በሥራ ላይ የሚያውል ሲሆን፣ አፈጻጸማቸውም የበለጠ ውጤታማ የሚሆነው ለፕሮግራሞች፣ ለፕሮጀክቶችና ለመደበኛ ተግባራት ማስፈፀሚያ የሚያስፈልጉ የፋይናንስ፣የሰው ሃይልና የማቴርያል ሃብቶች በተቀናጀ ዕቅድ ሲመራ ነው፡፡

የአገራችን የመንግሥት ፋይናንስ አስተዳደር ከ1983 ዓ.ም. በፊት በተበታተነ መልክ የሚሠራና ግልጽና ውጤታማ ያልነበረ፣ የተሟላ የህግ ማዕቀፍም ያልነበረው ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት ፋይናንሱን በማስተዳደርና በመቆጣጠር በኩል ከፍተኛ ክፍተቶች ነበሩበት፡፡

በአለፉት ዓመታት የፋይናንስ አስተዳደሩን ለማሻሻል በርካታ ስራዎች የተከናወኑ ቢሆንም ከሌሎች አገሮች ተሞክሮ ጋር ሲታይ የአገራችን የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር የበለጠ ውጤታማ ለማድረግ የማሻሻያ ስራዎች መሰራት እንደሚገባቸው በተለያዩ ጊዜያት የተካሄዱ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡ በተለይም ውጤታማ የሆነ የፕሮግራም በጀት ከመተግበር፣ ደረጃውን የጠበቀ የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር ከመዘርጋት፣ ዘመናዊ የመንግስት የሂሳብ አያያዝና የሪፖርት አቀራረብ ከመተግበር፣ የመንግስትን ገንዘብ ከብክነት ለመከላከል የሚያስችል ጠንካራ የውስጥ ኦዲት ከማቋቋም፣ግልጽና ውጤታማ የግዢና የንብረት አስተዳደር ስርዓት ከማስፈን፤ የፋይናንስ ስራውን የሚደግፍ ዘመናዊ የመረጃ ስርዓት ከመዘርጋት እና አሰራሩን ከማጠናከር አኳያ ወደፊት ብዙ የሚሰሩ ስራዎች በመኖራቸው ምክንያት ግልጽ የሆነ የማስፈጸሚያ ስትራቴጂ ዕቅድ መንደፍ ያስፈልጋል፡፡

በዚህ መሰረት የመንግሥት ፋይናንስ አስተዳደር ራዕይና ግቦች ያሉት ስትራቴጂ ተቀርጾለት ቢመራ ውጤታማ ይሆናል በሚል ታሳቢ ይህ የስትራቴጂ ሰነድ ተዘጋጅቷል፡፡

## 1.1 የትኩረት አቅጣጫዎች

### 1.1.1 ራዕይ (Vision)

#### ሀ. የሚኒስቴሩ ራዕይ

"በአገራችን ፐብሊክ ሰርቪስ ውስጥ በልቀቱና በውጤቱ መሪ ተቋም መሆን"

### ለ. የስትራቴጂው ራዕይ

“የአገራችንን የመንግሥት ፋይናንስ አስተዳደር ይበልጥ በማሻሻል በስትራቴጂው ዘመን መጨረሻ ላይ ከአፍሪካ የላቀ የፋይናንስ አስተዳደር ስርዓት መሆን ነው”

## 1.1.2 ተልዕኮ (Mission)

### ሀ. የሚኒስቴሩ ተልዕኮ

- የተቋም አቅም ግንባታ፣
- ፊስካል ፖሊሲ፣
- መንግስት ፋይናንስ አስተዳደር እና
- የውጪ ሀብት ማሰባሰብና አጋርነት ማጎልበት

### ለ. የስትራቴጂው ተልዕኮ

“የአገራችንን የመንግሥት ፋይናንስ አስተዳደርን ዘመናዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ በማድረግ ግልፀኝነትን፣ ተጠያቂነትንና ፍትሃዊነት የሚያሰፍን እና ለኢኮኖሚ ዕድገት አጋዥ እንዲሆን ማድረግ ነው ”

## 1.2 የስትራቴጂው ዓላማ

### 1.2.1. የስትራቴጂው ዋና ዓላማ

የስትራቴጂው ዋና ዓላማ የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር የአገሪቱን የልማት ስትራቴጂ መሰረት ያደረገ ዘመናዊ፣ ቀልጣፋ፣ተጠያቂነት የሰፈነበትና ውጤታማ እንዲሆን ለማስቻል ነው፡፡

### 1.2.2. የስትራቴጂው ዝርዝር ዓላማዎች

ስትራቴጂው የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች አሉት፡-

ሀ) ውጤታማ የሆነና በመከከለኛ ጊዜ የልማት ዕቅድ ላይ የተመሰረተ የፕሮግራም በጀት ስርዓት ለማስፈን፣

ለ) የጥሬ ገንዘብ ክፍያና አስተዳደር ስርዓት ለማሻሻል፣

ሐ) የመንግስት ፋይናንስ ሪፖረት አቀራረብ አለማቀፍ ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን በማድረግ

ጥራቱን የጠበቀ፣ የተሟላና ተጠያቂነትን የሚያሰፍን ለውሳኔ ሰጪው አካል የፋይናንስ መረጃን በማቅረብ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓቱን ለማጠናከር፣

መ) የተቀናጀ የመንግሥት ፋይናንስ አስተዳደር የመረጃ ሥርዓት (IFMIS) የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር የምዝገባ ስርዓት እንዲሆን ለማስቻል፣

ሠ) የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር መረጃዎች ለዜጎች ተደራሽን እንዲሆኑ በማድረግ ግልጽነትን፣ ተጠያቂነትንና አሳታፊነትን ለማስፈን፣

ረ) የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር በዘመናዊ ስርዓት እንዲመራ ለማድረግ ፣

ሰ) በመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር ተግባራት ላይ የሚሳተፉ ባለሙያዎች የሙያ ደረጃ እና ብቃት ለማሳደግ፣

ሸ) የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር የማሻሻያ ስራዎች ስርዓተ ፆታን እና ልዩ ልዩ ፍላጎት ያላቸውን የማህበረሰብ ክፍሎች አሳታፊነት እና ተጠቃሚነት ማሳደግ፣ ነው፡፡

## 1.3 የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር ትርጓሜ

የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር በተለያዩ ዓለም አቀፍ ተቋማት እና ሃገሮች የተለያየ ትርጓሜ የተሰጠው ሲሆን በዚህ ስትራቴጂ የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር ማለት የፊሲካል ፖሊሲን፣ በጀት አስተዳደርን፣ የጥሬ ገንዘብ ክፍያና አስተዳደርን፣ የብድር አስተዳደርን፣ የሂሳብ አያያዝና ሪፖርትን አቀራረብን፣የኦዲትና የውስጥ ቁጥጥርን፣ የግዥና ንብረት አስተዳደርን እና ሌሎች ተያያዥ የክትትል ስራዎች ማለት ነው፡፡

## 1.4 የስትራቴጂው ወሰን

ይህ ስትራቴጂ የሚተገበረው ከ2010 እስከ 2014 በጀት ዓመት ሲሆን የትግበራ መስኮቹ የፊሲካል ፖሊሲ፣ ታክስ ፖሊሲ፣ የፕሮግራም በጀት፣ የጥሬ ገንዘብ ዝግጅትና የክፍያ አስተዳደር፣ የብድር አስተዳደር፣ የመንግስት የሂሳብ አያያዝና ሪፖርት አቀራረብ፣ የውስጥ ኦዲትና ቁጥጥር፣ የግዥ እና ንብረት አስተዳደር፣ የመረጃና የክትትል ስርዓት እና የመንግስትና የግል አጋርነት ያጠቃልላል፡፡

# 2. የመንግሥት ፋይናንስ አስተዳደር የማሻሻያ ስራዎች አጀማመር

ከ1983 በጀት ዓመት በፊት የአገራችን የመንግሥት ፋይናንስ አስተዳደር የተሟላ የሕግ ማዕቀፍ ስላልነበረው ፋይናንሱን በማስተዳደርና በመቆጣጠር በኩል ከፍተኛ ችግሮችና ክፍተቶች ነበሩበት፡፡ በዚህም ምክንያት የተነሳ በ1987 በጀት ዓመት የጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ከፍተኛ

የመንግሥት ኃላፊዎች፣ ባለሙያዎች እና ኢንተርናሽናል አማካሪዎች የሚገኙበት አንድ አጥኚ ቡድን እንዳቋቋመ እና ቡድኑም ለሁለት ዓመት ጥናቱን ካከናወነ በኋላ የመንግሥት የፋይናንስ አስተዳደርን አስመልክቶ የሚከተሉትን ዋና ዋና ችግሮችና የመፍትሄ ሃሣባቸው ከዚህ በታች በተመለከተው መሰረት መለየቱን የመንግስት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ሪፎርም ፕሮግራሞች ጥናት ያስረዳል፡፡

- የመንግሥት ፋይናንስ አስተዳዳርና ቁጥጥር ወጥነት ባለው መልክ መምራት አለመቻሉ፣
- የመንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር ወጥ የሆነና የተሟላ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያዎች ያልወጡለት ስለሆነ ፋይናንሱን በማስተዳደርና በመቆጣጠር ላይ ችግር እንዳለው፣
- የበጀት ዝግጅት የረዥም ጊዜ የፋይናንስና የልማት ዕቅድን ያልተከተለ፣ ከስትራቴጂክ ዕቅድ ጋር የማይገናኝ፤ የበጀት የጊዜ ሰሌዳ (budget calendar) የሌለው፤ በጀቱ ያስገኘው ውጤት የማይገመገምበት መሆኑ፣
- የክፍያ ሥርዓቱ የጥሬ ገንዘብ ፍላጐትን ያልተከተለ፤ የበጀት አንድ አሥራ ሁለተኛ እየተሰላ ክፍያ የሚተላለፍበት ሁኔታ መኖሩ፣ አንዳንድ መ/ቤቶች በራሳቸው ትዕዛዝ የባንክ ሂሣብ እንደሚከፍቱ፣ በአንዳንድ መ/ቤቶች የባንክ ሂሣብ ውስጥ ከፍተኛ ጥሬ ገንዘብ (idle cash) ተከማችቶ እንደሚቀይ ፣
- የተጠቃለለና ኦዲት የተደረገ የመንግሥት ሂሣብ እጅግ ወደኋላ የቀረ (ከ4-5 ዓመታት) በመሆኑ በፋይናንስ ቁጥጥሩ ሥራ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ማሳደሩ፣ አገሪቱ ኋላ ቀር የነጠላ ሂሣብ አሠራር (single entry) እንደምትከተል፣ ይህ ደግሞ ጥሬ ገንዘብ ላልሆኑ ንብረቶችና ሂሣብ ምዝገባ አመቺ አለመሆኑ፣
- የመንግሥት ንብረትን ተቆጣጥሮ ሥራ ላይ በማዋሉ ረገድ ከፍተኛ ድክመቶች መኖራቸው፣የንብረት ምዝገባ፣ ቆጠራ፣ ወዘተ... ትኩረት ያልተሰጠው መሆኑ፣
- ገንዘብ ሚኒስቴር የፋይናንስ አስተዳደሩን ለማስከበር ህጋዊ አቅሙ ደካማ መሆኑ፣
- ከውጪ የሚመጣውን የብድርና ዕርዳታ ገንዘብ በአግባቡ ተቆጣጥሮ ለታሰበለት ዓላማ በማዋል ረገድ ከፍተኛ ድክመቶች መኖራቸው፣
- በተለያዩ መ/ቤቶች የውስጥ ኦዲት የሥራ እንቅስቃሴ ደካማ መሆኑ፣ የውስጥ ኦዲት ቅድመ ክፍያ ማረጋገጥ ላይ ብቻ ማተኮሩ፣ በአንዳንድ መ/ቤቶች የውስጥ ኦዲት መዋቅሩም አለመኖሩ፣ በገንዘብ ሚኒስቴርና በመ/ቤቶች የውስጥ ኦዲት መካከል ያለው ግንኙነት ግልጽ አለመሆኑ፣ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱ በአግባቡ ያልተዘረጋና ለብክነት የሚዳርግ መሆኑ፣
- የዋናው ኦዲተር በሰው ኃይል እጥረትና በሌሎች ምክንያቶች የኦዲት ሥራቸውን በወቅቱ ሊወጡ ያለመቻላቸው፣ በሚያቀርቡትም ሪፖርትና ግኝቶች ላይ የሚወሰድ እርምጃ አለመኖሩ፣

- በመንግሥት የፋይናንስ አስተዳደሩ ከፍተኛ ብቃት ያለው የባለሙያ እጥረት መኖሩ፣ የሂሣብ ባለሙያዎችንና (አካውንታንቶችንና) ኦዲተሮችን የማብቃት የሥልጠና ሥርዓቶች አለመኖራቸው የሚሉት ይገኙበታል፡፡

ከላይ የተዘረዘሩትን የጥናቱን ውጤቶች መሠረት በማድረግ በአገሪቱ የሚገኘውን የሲቪል ሰርቪስ ሚናና አወቃቀር በአዲስ መልክ ማሻሻል ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ የመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ሪፎርም ፕሮግራም ከሲቪል ሰርቪስ ሪፎርም አምስቱ ንዑሳን ፕሮግራሞች አንዱ ሆኖ እንዲቀረጽ ተደረጓል፡፡ የመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ማሻሻያ ሪፎርምም ዓላማዎችና ግቦችን ተቀርጾለት እና በተለያዩ ፕሮጀክቶች በማደራጀት የማሻሻያው ስራዎች እንዲሰሩ ተደርጓል፡፡

የወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ማሻሻያ ፕሮግራም የመንግሥት ፋይናንስ አስተዳደርን ውጤታማ ለማድረግና፣ ግልፅነትና ተጠያቂነትን ለማስፈን የተለያዩ 12 ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ ስራ ላይ አውሏል፡፡

ፕሮጀክቶቹም የመንግሥት ፋይናንስ የህግ ማዕቀፍ ማሻሻያ፣የበጀት አስተዳደር ማሻሻያ፣ የመንግሥት ወጪ ዕቅድ ማሻሻያ፣ የጥሬ ገንዘብ አስተዳደርና ክፍያ አሠራር ማሻሻያ፣ የመንግሥት ሂሣብ ማሻሻያ፣ የውስጥ ኦዲት ማሻሻያ፣ የተቀናጀ የፋይናንስ መረጃ ሥርዓት ማሻሻያ፣ የመንግሥት ግዥ ሥርዓት ማሻሻያ፣ የመንግሥት ንብረት አስተዳደር ማሻሻያ፣ የሂሣብና ኦዲት ሙያ ማሻሻያ፣ የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት እና የውጪ ኦዲት ማሻሻያ ሲሆኑ ከእነዚህ የማሻሻያ ፕሮጀክቶች መካከል የመጀመሪያዎቹ አስራ አንዱ በማሻሻያ ፕሮግራሙ የቅርብ ክትትል የሚደረግባቸው ሲሆን፣ ያስገኙት ውጤቶች በሚቀጥለው ምዕራፍ በዝርዝር ቀርቧል፡፡

# 3. የመንግሥት ፋይናንስ አስተዳደር ማሻሻያ ስራዎችና የተገኙ ውጤቶች

## 3.1. የሕግ ማዕቀፍ

የመንግሥት ፋይናንስ አስተዳደር ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመምራት ሁለት አዋጆች የወጡ ሲሆን እነሱም የፌዴራል መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር እና የመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጆች ናቸው፡፡ እነዚህን አዋጆች ተከትለው የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር ደንብ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ጸድቋል፡፡ አዋጆቹንና የፋይናንስ ደንቡን ለማስፈጸምና የበለጠ ለማብራራት ብዛታቸው 16 ያህል የመንግሥት የፋይናንስ፣ ግዥና ንብረት አስተዳደር መመሪያዎች ወጥተዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በአዋጆቹ፣ ደንብ እና የአፈፃፀም መመሪያዎች የተገለጹትን ዋና ዋና ተግባራትን ሂደትና ዝርዝር አፈጻጸም የሚያመለክት እና ሠራተኞችን/ፈጻሚዎችን ቅልጥፍና እንዲጨምር ሊያግዝ የሚችል የአሠራር ማንዋሎች ተዘጋጅቷል፡፡

እነዚህም ማንዋሎች የፕሮግራም በጀት፣ የጥሬ ገንዘብ አስተዳደርና የክፍያ አሠራር፣ የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት፣ የውስጥ ኦዲት፣ የክዋኔ ኦዲት፣ የመንግሥት ግዥ አፈፃፀም፣ የመንግሥት ቋሚ ንብረት አስተዳደር፣ የስቶክ ማኔጅመንና የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት ያጠቃልላል፡፡ ይህም የአገራችን የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር በተሟላ የህግ ማዕቀፍና ተቋማዊ አሰራር እንዲመራ አስችሏል፡፡

## 3.2. የመካከለኛ ዘመን ፊሲካል ማዕቀፍ እና የፕሮግራም በጀት

### 3.2.1. የመንግሥት ገቢ እና ወጪ ዕቅድ ማሻሻያ

የመንግስት ገቢን ለማሻሻል በርካታ የማሻሻያ ተግባሮች የተከናወነው ሲሆን ዋና ዋናዎቹ፡-

- የታክስ ፖሊሲውንና አስተዳደሩን ለማሻሻል በርካታ ጥናቶችንና ግምገማዎችን ተደርገው የገቢ ግብር፣ የታክስ አስተዳደር፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ፣ የኤክሣይስ ታክስ፣ የተርን ኦቨር ታክስ እና የኢንቨስትመንት ማበረታቻ አዋጆችንና ደንቦች ተዘጋጅተውና በየጊዜው ተሻሽለው ተግባራዊ ተደርገዋል፣
- ለታክስ ፖሊሲው እና የመንግስትንና የግል ዘርፉን አጋርነት የሚመሩና የሚያስፈፅሙ የስራ ክፍሎች ተደራጅተው ወደስራ ተገብቷል፣
- የመንግስትንና የግል ዘርፍ አጋርነት የፖሊሲ ሠነድ ተዘጋጅቶና አዋጅ ወጥቷል፣

በወጪ ዕቅድ ፕሮጀክት ስር የመንግሥት ኢንቨስትመንትና የመንግሥት ወጪ ፕሮግራሞች የነበሩ ሲሆን ዓላማውም በፖሊሲዎች፣ በዕቅድና በበጀት መካከል ሊኖር የሚገባውን ቅንጅት ለማሻሻል የተቀረጸ ነበር፡፡ በዚሁ መሰረትም የወጪ ዕቅድን ለማሻሻል በተሰሩ ሥራዎች የሚከተሉት ዋና ዋና ውጤቶች ተገኝተዋል፡-

- የመንግሥት ኢንቨስትመንት ፕሮግራም ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን ከዓመታዊ በጀት ጋር በማቀናጀት የመካከለኛ ዘመን ዕቅድ ለማዘጋጀት ተችሏል፤ የኢንቨስትመንት ፕሮግራሞች ቅደም ተከተል እንዲይዙ ተደርጓል፣ ለዓመታዊ የካፒታል በጀት ዝግጅት መሠረት በመሆን አገልግሏል፣
- የመንግሥት ወጪ ዕቅድ ማሻሻያ ስራዎች ተከናውነው የመንግሥት ወጪ ፕሮግራም ማለትም የካፒታልና የመደበኛ ወጪ ዕቅድ በአንድ ላይ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፣
- የፌዴራል መንግሥት ኢንቨስትመንት ፕሮግራም (PIP) በየዓመቱ ለአምስት ተከታታይ ዓመታት (1991-93፣ 1992-94፣ 1993-95፣ 1994-96፣ 1995-97) ሰነዶች ተዘጋጅተው ስራ ላይ ውለዋል፣
- በማክሮ ኢኮኖሚ እና ፊስካል ማዕቀፍ የሦስት ዓመት ተንከባላይ የገቢና ወጪ ዕቅድ በማዘጋጀት ዓመታዊ በጀት ዝግጅት በመካከለኛ ዘመን ዕቅድ ላይ የተመሰረተ እንዲሆን

ተደርጓል፣በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ 648/2001 ሕጋዊ መሰረት አግኝቶ በየበጀት ዓመቱ እየተዘጋጀ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቦና ፀድቆ እንዲተገበር ተደርጓል፡፡

### 3.2.2. የመንግስት በጀት ዝግጅትና አስተዳደር

በበጀት ማሻሻያዎች የተገኙ ዋና ዋና ውጤቶች :-

- የዝርዝር የወጪ አርዕስት በጀት /line Item Budgeting/ ላይ ማሻሻያ በማድረግ በወጪ ማዕከል /Cost center/ ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ተደርጓል፣
- በሀገር አቀፍ ደረጃ ወጥ የሆነ የበጀት አወቃቀር እንዲሁም የሂሳብ አወቃቀር ሥርዓት እንዲኖር በማድረግ የመደበኛና የካፒታል በጀቶች እንዲቀናጁ እና በአንድ ላይ እንዲሰሩ ተደርጓል፣
- የበጀት አሰራር በመረጃ ሥርዓት እንዲሆን ተደርጓል፣
- በግብዓት ላይ ከተመሰረተ የበጀት አሰራር ወደ ውጤት ላይ ያተኮረ የፕሮግራም በጀት ሥርዓት እንዲሸጋገር በማድረግ ከ2004 ጀምሮ በፌዴራል መንግስት ባለበጀት መ/ቤቶች ደረጃ እንዲተገበር እንዲሁም የስርዓተ ፆታ ጉዳይ አሰራር ተካቶ መተግበር ተጀምሯል፣
- በክልል ደረጃ በዝርዝር ወጪ አርዕስት ላይ የተመሰረተ የበጀት አሰራር ተተግብሯል፣

## 3.3. የመንግሥት ጥሬ ገንዘብ፣ ክፍያ እና ብድር አስተዳደር ሥርዓት

### 3.3.1. የመንግሥት ጥሬ ገንዘብ አስተዳደር እና ክፍያ ሥርዓት

በመንግሥት ጥሬ ገንዘብ አስተዳደርና ክፍያ ማሻሻያ የተገኙ ዋና ዋና ውጤቶች:-

- በመሰሪያ ቤቶች እና በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ደረጃ የመንግስት የጥሬ ገንዘብ ዕቅድ እንዲዘጋጅ በማድረግ በዜሮ ሚዛን የክፍያ ዘዴ እንዲፈጸም ተደርጓል፣
- የባንክ ሂሳብ ቁጥር መደቦችና አይነትን እንዲወሰን በማድረግ አላስፈላጊ የጥሬ ገንዘብ ክምችት እንዲቀንስ ተደርጓል፣
- የመንግስት መ/ቤቶች ሠራተኞች የደመወዝ ክፍያ በባንክ በኩል ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሆኗል፣
- የመንግስት ጥሬ ገንዘብ አስተዳደርና ክፍያ ስርዓት በመረጃ ሥርዓት እንዲደገፍ ተደርጓል፣

### 3.3.2. የመንግሥት ብድር አስተዳደር ሥርዓት

- የDebt Portfolio Analysis የጠፉ ብድሮች እና ስጋትን በማካተት በየዓመቱ ተዘጋጅቷል፣ የመካከለኛ ዘመን የብድር ስትራቴጂ (2005-2009) ተቀርጾ በስራ ላይ ውሏል፤ ከሁለተኛው ምዕራፍ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ጋር ለማቀናጀት እንዲቻል ክለሳ ተካሂዶ ተግባራዊ ተደርጓል፣

- የዕዳ ጫና ትንተና (Debt Sustainability Analysis) ሰነድ ተዘጋጅቶ የብድር አስተዳደር ስርዓቱ በስትራቴጂ እንዲመራ ተደርጓል፣

- የአገሪቱ የብድር አስተዳዳር ሁኔታ ግምገማ /Debt Management Performance Assement/ ተከናውኗል፣

- በየሩብ ዓመቱ የPublic Sector Debt Statiscal Bulletin ተዘጋጅቷል፣

- የአገሪቱ የብድር መረጃ የሚመዘግቡበት ስርዓት ከነበረበት DMFAS 5.3 ወደ DMFAS 6 እንዲሻሻል ተደርጓል፣

- ለመንግስት ባለበጀት መስሪያ ቤቶችና የልማት ድርጅቶች በመልሶ ማበደር የተላለፉ የብድር መረጃዎች ተሟልተው እንዲያዙ ተደርጓል፣

## 3.4. የመንግስት የሂሳብ አያያዝና ሪፖርት አቀራረብ ሥርዓት

መንግስት የሂሳብ አያያዝ የማሻሻያ የተገኙ ዋና ዋና ውጤቶች፡-

- የመንግስት ሂሳብ ቀድሞ ከነበረበት የነጠላ ሂሳብ ምዝገባ ወደ ጣምራ ሂሳብ ምዝገባ በመቀየሩ ለመንግስት ፖሊሲ ውሳኔ አመቺ የሆነ የፋይናንስ መረጃ ማቅረብ ተችሏል፣

- የመንግስት መስሪያ ቤቶች ሂሳባቸውን ዘግተው የሚያስመረምሩበትና የሚጠየቁበት የ"Self Accounting and Reporting" ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሆኗል፣

- የመንግስት ሂሳብ አወቃቀር /Chart of Account/ የዓለም አቀፍ ደረጃ (GFS-2001) ጠብቆ እንዲሰራ አደርጓል፣

- የመንግስት ሂሳብ አያያዝ በመረጃ ስርዓት እንዲደገፍ ተደርጓል፣

- ከ4-5 ዓመታት ያህል ሳይዘጋና ሳይመረመር ወደ ኋላ ቀርቶ የነበረው የመንግስት ሂሳብ በየበጀት ዓመቱ እንዲዘጋ በማድረግ መመርመር ተችሏል፣

- የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር የፑል አሰራር ስርዓት በወረዳዎች ተተግብሯል፣

## 3.5. የመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር

በመንግሥት ግዥ እና ንብረት ማሻሻያ የተገኙ ዋና ዋና ውጤቶች፡-

- የግዥ መደበኛ የጨረታ ሰነዶች (SBD) ተዘጋጅተው በፌዴራልና በክልሎች በሥራ ላይ እንዲውሉ ተደርጓል፣
- የመንግሥት የግዥ ሥርዓት ባልተማከለ እና በተማከለ መንገድ እንዲመራ ተደርጓል፣
- በመንግሥት ግዥ አፈፃፀም እና ንብረት ማስወገድ ሂደት ከተጫራቾች/አቅራቢዎች የሚቀርብ አቤቱታን አጣሪና ውሳኔ ሰጪ ቦርድ ተቋቁሟል፣
- የአቅራቢዎች ምዝገባ በመረጃ መረብ (web based) እንዲሆን ተደርጓል፣
- ከ220 በላይ ለሚደርሱ ዕቃዎች አገር አቀፍ ስታንዳርድ የማውጣትና የተዘጋጀውን ስታንዳርድ በሁሉም የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች እንዲተገበር ተሰራጭቷል፣
- የመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ፕሮፌሽናል ሰርቲፊኬሽን ሥልጠና በሶስት ደረጃዎች (Basic, Essential and Advanced levels) በመሰጠት ላይ ይገኛል፣
- በፌደራል መንግስት መ/ቤቶች የግዥ ኦዲት እየተደረገ ይገኛል፣

## 3.6. የውስጥ ኦዲት

በውስጥ ኦዲት መሻሻያ የተገኙ ዋና ዋና ውጤቶች፡-

- በአገር አቀፍ ደረጃ የውስጥ ኦዲት ከቅድመ-ኦዲት ወደ ድህረ-ኦዲት ስርዓት እንዲሸጋገር ተደርጓል፣ለዚሁም አፈፃፀም አደረጃጀት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ተደርጎል፣
- የውስጥ ኦዲተሮች የሙያ ሥነ ምግባርና ደረጃዎች ያካተተ የውስጥ ኦዲት መመሪያ ወጥቶ በሥራ ላይ እንዲውል ተደርጎል፣
- የወረዳ ኦዲት ኮሚቴ መመሪያ በማዘጋጀት ከ400 በላይ በሆኑ ወረዳዎች ኮሚቴው እንዲቋቋም ተደርጎ የኦዲት ክትትል ስራዎች እንዲጠናከሩ ተደርጓል፣
- የውስጥ ኦዲተሮች ነፃ እና ገለልተኛ ሆነው ስራዎቻቸውን በጥራት እንዲያከናውኑ ለማስቻል በፌደራል ደረጃ አስተዳደራዊ ተጠሪነታቸው ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ተደርጓል፡፡

## 3.7. ዘመናዊ የመረጃ ስርዓት አጠቃቀም

በመረጃ ስርዓት ማሻሻያ የተገኙ ዋና ዋና ውጤቶች፡-

- የበጀት የመረጃ ሥርዓትን (BIS) እና ለሂሣብ አሠራሩ የበጀት፣ ክፍያና ሂሳብ (BDA) የመረጃ ሥርዓቶች ለምተው ተግባራዊ ተደርጓል፣
- የተቀናጀ የበጀትና የወጪ ስርዓት (IBEX) ለምቶ በፌዴራል፣ በክልል፣ በዞኖችና ወረዳዎች መንግስት ባለበጀት መሥሪያ ቤቶች ሥራ ላይ ውሏል፣
- የተቀናጀ የፋይናንስ አስተዳደር የመረጃ ሥርዓት (IFMIS) ዘጠኝ ሞጁሎችና አንድ ቻርት ኦፍ አካውንት በማዘጋጀት ከ2003 በጀት ዓመት ጀምሮ በፌዴራል ደረጃ በ 32 መ/ቤቶች በመተግበር ላይ ይገኛል፣

## 3.8. የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት

በፋይናንስ ግልፅነትና ተጠያቂነት የተገኙ ዋና ዋና ውጤቶች፡-

- በሀገሪቱ በሚገኙ በሁሉም ወረዳዎች/ከተማ አስተዳደሮች የበጀትና ወጪ እንዲሁም የመሰረታዊ አገልግሎት አሰጣጥ መረጃ በተዘጋጁት ቴምፕሌቶች አማካኝነት ወቅቱን ጠብቆ ለዜጎች ተደራሽ እንዲሆኑ ተደርጓል፣
- በፌዴራልና በክልሎች/ከተማ አስተዳደሮች ደረጃ የብዙሃን መገናኛን (ቴሌቪዥንና የሬዲዮ) በመጠቀም የመንግስት በጀት መረጃን ተደራሽ በማድረግ የዜጎችን ግንዛቤ ማሳደግ ተችሏል፤
- በመንግስት በጀት መረጃ ላይ ለ2.4 ሚሊያን ከክልል የተወጣጡ ልዩ ልዩ የማህበረሰብ ተወካዮች ግንዛቤ እንደኖራቸው ተደርጓል፤
- የዜጎች የቅድመ-በጀት ውይይት መተግበሪያ ማኑዋል ተዘጋጅቶ በ350 ያህል ወረዳዎች በአስፈጻሚው አካልና በዜጎች መካከል የቅድመ በጀት ውይይቶች ተደርገዋል፣
- ከ2010 በጀት ዓመት ጀምሮ የፋይናንስ ግልፅነትና ተጠያቂነት ስርዓት በፌዴራል ደረጃ ተግባራዊ ማድረግ ተጀምሯል፡፡

# 4. ልማታዊ መንግስት እና የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር

የአንድ አገር መሠረታዊ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በዋናነት በመንግሥትና በግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ በሚቀርቡ ምርትና አገልግሎቶች መጠንና ጥራት ይወሰናል፡፡ ይህን ለማድረግ ሁለቱ አካላት ድርሻቸውን መወጣትና መደጋገፍ ይኖርባቸዋል፡፡ በኢኮኖሚ ጠበብት አመለካከት መንግሥት

እና የግሉ ዘርፍ ለኢኮኖሚ ዕድገት ያላቸውን ወሳኝነት የማበላለጥ ወይም ለአንዱ ቅድሚያ የመስጠት አዝማሚያዎች የተከሰቱ ቢሆንም በአጭር ጊዜ ከድህነት ተላቀው ብልፅግናን የተላበሱ አገሮች ተሞክሮ የሚያሳየው የመንግሥትን ሚና ወሳኝ መሆኑን ነው፡፡ በመሰረቱ ማንኛውም ለልማት የቆመ መንግስት ሁሉ ልማታዊ መንግስት ነው ማለት ይቻላል፡፡ ሆኖም በኢኮኖሚ ልማት ንድፈ ሃሳብ ልማታዊ መንግስት በመባል የሚታወቁት የምስራቅ ኤሽያ አገሮች በተለይም የኮሪያና የታይዋን መንግስታት ዓይነት የልማት አቅጣጫ የሚከተሉት ሲሆኑ፣ ይህ የልማታዊ መንግስት ኢኮኖሚ ሞዴል እነዚህ አገራትን በአጭር ጊዜ ውስጥ ከድህነት ተላቀው በኢኮኖሚያቸው የበለጸጉ አገራትን እንዲቀላቀሉ አስችሏቸዋል፡፡ ለዚህ ውጤት ደግሞ መንግስታት በኢኮኖሚው እንቅስቃሴ ውስጥ የነበራቸው ሚና የጎላ ነበር፡፡ በአጠቃላይ ሲታይ ልማታዊ መንግስታት በ3 ዋና ባህሪት ከሌሎቹ ይለያሉ፡፡ እነዚህም በመጀመሪያ ልማትን የህልውናቸው ጥያቄ ያደረጉ መንግስታት በመሆናቸው ከድህነት ለመውጣት ብርቱ ትግል ያደርጋሉ፤ በሁለተኛነት መንግስት ባለሃብቱን በሙሉ ልብ የመደገፉ መርህ እንደተጠበቀ ሆኖ ከባለሃብቱ ፖለቲካና አስተሳሰብ ተጽዕኖ ነፃ በመሆን የሚንቀሳቀስ ሲሆን፣ በሶስተኛነት ደግሞ ልማታዊ መንገዱ ለተከታታይ ዓመታት ቀጣነት እንዲኖረው ልማታዊነት የአስተሳሰብ የበላይነቱን ያረጋገጠበት ሥርዓት እንዲሆን ያደርጋሉ፡፡

በአገራችንም ከላይ የተዘረዘሩትን ሦስት የልማታዊ መንግስት ባህሪያት በመያዝ እና በተጨማሪም በአራተኛነት ዲሞክራሲን በአገሪቱ ማስፈን የሞት ሽረት ጉዳይ አድርጎ በመውሰድ እንዲሁም በአምስተኛነት የህዝብ ተሳትፎና ባለቤትነትን የልማታዊ መንግስቱ ባህሪያት አድርጎ በመውሰድ መንግስት የልማታዊ መንግስት ኢኮኖሚ ሞዴል መከተል ከድህነትና ከኋላ ቀርነት በማላቀቅ አገሪቱን በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ መካከለኛ እና በሂደትም ወደ በለፀገ ኢኮኖሚ ሊያሸጋግር እንደሚችል በመረዳት ከአገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር ስርዓቱን በተለይ ከ1994 ዓ.ም. ጀምሮ በመተግበር ላይ ይገኛል፡፡ በልማታዊ መንግስት ስርዓት መንግስት በኢኮኖሚው ውስጥ ያለው ሚና ከፍተኛ በመሆኑ፣ በመንግስት በኩል ከፍተኛ የሆነ ሀብት ወጪ ተድርጎ ኢኮኖሚውን የማንቀሳቀስ፣ የገበያ ክፍተት ባለበት ክፍተቱን የመሸፈን ተግባር ይከናወናል፡፡ ይህም ውሱን የሆነውን የመንግስት ሀብት በቁጠባና በብቃት ማስተዳደርና ጥቅም ላይ ማዋልን የሚጠይቅ ይሆናል፡፡ ለዚህም የመንግስትንም ሆነ የግሉን ዘርፍ የማስፈጸም አቅም መገንባት እና የፋይናንስ አቅም በከፍተኛ ደረጃ ማሳደግን ይጠይቃል፡፡ ለዚህም ባለፉት ተከታታይ 15 ዓመታት ድህነት ተኮር ለሆኑት የመሰረታዊ አገልግሎቶችና እና የመሰረተ ልማት ፕሮግራሞች መንግስት ከፍተኛ በጀት በመመደብ፣ የገበያ ክፍተት ባለበት ላይ በቀጥታ ጣልቃ በመግባት፣ የግሉን ዘርፍ ለማበረታታት የሙያ ድጋፍ በመስጠት፣ ብድር በማመቻቸት፣ የግብር እፎይታን ጨምሮ ለሚያካሂዷቸው ኢንቨስትመንቶች የቀረጥ ነፃ መብት ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረግ ዘርፍን የመደገፍ ስራ ተሰርቷል፡፡

ለዚህም በአገራችን በተለይ ባለፉት 15 ዓመታት በሁሉም ዘርፍ መጠነ ሰፊ የአቅም ግንባታ ማሻሻያ ፕሮግራሞች ተነድፈው በመተግበራቸው የአገሪቱ የማስፈጸም አቅም በከፍተኛ ደረጃ

ተሻሽሏል፡፡ ለዚህም በተለይ በትምህርት፣ በጤና፣ በመንገድና በመጠጥ ውሃ ተደራሽነትና ሽፋን፤ በኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት፣ በግብርና ምርት ዕድገት፣ በኢንዱስትሪ መስፋፋት ወዘተ የተገኙት ዕድገቶች በአመዛኙ መንግስት በቅድሚያ ተነሳሽነት ያከናወናቸው ናቸው፡፡ ይህም በመሆኑ ባለፉት ተከታታይ አስር ዓመታት የአገሪቱ ኢኮኖሚ ከአስር በመቶ በላይ በማደግ ከዓለም ቀዳሚ የኢኮኖሚ ዕድገት ከተመዘገበባቸው ጥቂት አገራት አንዷ ለመሆን ከመብቃታችን በተጨማሪ የህዝባችን የድህነት ምጣኔ ከግማሽ በላይ ቀንሷል፡፡

## 4.1. የመንግሥት ገቢ ማሻሻያ

የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓቱን በማሻሻል የማስፈጸም አቅሙን ለመገንባት በተሰሩ ስራዎችም በፌዴራልና በብሄራዊ መንግስታት እስከ ታችኛው የአስተዳደር እርከን ድረስ መጠነ ሰፊ የፋይናንስ ህግና የአሰራር ስርዓት ማሻሻዎች የተደረጉ ሲሆን፣ በዚህም የመንግስት ወጪ አስተዳደሩ በዘመናዊና ቀልጣፋ ከመሆኑም በተጨማሪ የመንግስት ገቢን በከፍተኛ መጠን ሊያድግ ችሏል፡፡ በተለይም ከ1994 በፊት በተካሄዱ የመንግሥት ገቢ ማሻሻያ እርምጃዎች የወራሽነት ባህሪ የነበራቸውን የታክስ ማስከፈያ መጣኔዎች ዝቅ በማድረግ፣ የታክስ መሠረቱን በማስፋትና አስተዳደሩን በማሻሻል እንዲሁም ያልተማከለ የመንግሥት ፋይናንስ አስተዳደር ዕውን በማድረግ የሀገር ውስጥ ገቢን ለማጐልበት ጥረት ተደርጓል፡፡ ሆኖም የተወሰዱት እርምጃዎች የሚፈለገውን የፋይናንስ አቅም ማመንጨት ባለመቻላቸው ተጨማሪና የተጠናከሩ የገቢ ፖሊሲና አስተዳደራዊ ማሻሻያዎችን ማድረግ ግዴታ ሆኗል፡፡

ታክስ የመንግሥት ዋናው የገቢ ምንጭ በመሆኑ ለውጤታማነቱ መሥራት ግዴታ ነው፡፡ የታክስ ፖሊሲው ተፈላጊውን ገቢ ከማመንጨት ባሻገር ሌሎች ዓላማዎችን ለማስፈፀም መዋል ይኖርበታል፡፡ መንግሥት የታክስ ፖሊሲው የዜጐችን የመሥራት ፍላጐት ለማበረታታት፣ የገቢ ልዩነት ለማጥበብ፣ የኢንቨስትመንትን አቅጣጫ ለመምራት፣ እንዲሁም ያልተፈለጉ ምርትና አገልግሎቶችን ለመቆጣጠር ይገለገልበታል፡፡ በአገራችንም ሥራ ላይ የዋሉ የታክስ ፖሊሲዎች በዋናነት ገቢን ለማሳደግ ትኩረት ያደረጉ ቢሆንም እነዚህን ተጓዳኝ የፖሊሲ መሣሪያዎች ተግባራዊ ለማድረግ ረድተዋል፡፡ በሌላም በኩል የታክስ ፖሊሲው የታክስ አስተዳደሩ ውጤታማ፣ የማያዳላና አስተዳደራዊ ብቃትን የሚያጐለብት እንዲሆን የማድረግ ሥራ ተከናውኗል፡፡

እነዚህንም የታክስ ፖሊሲ ዓላማና መርሆዎች ተግባራዊ ለማድረግ የተከናወኑ የታክስ ፖሊሲ ማሻሻያ እርምጃዎች የሚከተሉትን መሠረት ያደረጉ ናቸው፡፡ እነዚህም፡-

- በወጪ ንግድ ላይ ጥገኛ የሆነውን ገቢ በአገር ውስጥ የፍጆታ ታክሶች ላይ እንዲመሠረት ማድረግ፣
- የታክስ ጫናውን ከምርት ይበልጥ በፍጆታ ላይ ማሸጋገር፣
- የታክስ ጫናውን ከድሀው የህብረተሰብ ክፍል ይልቅ የተሻለ ገቢ ያለው እንዲሸከም ማድረግ፣

- ከፍተኛ የታክስ መጣኔን ከመጠቀም የታክስ መሠረቱን ማስፋት፣

- ለኢንቨስትመንት የተሰጡ የታክስ ማበረታቻዎችን መከታተልና አፈፃፀማቸውን በመገምገም በማሻሻያ እርምጃ መውሰድ፣

- ለታክስ አስተዳደሩ መሻሻል ከፍተኛት ትኩረት መስጠት ናቸው፡፡

እነዚህንም ተግባራዊ ለማድረግ መንግሥት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት የታክስ ማሻሻያ ፕሮግራም ዘርግቶ በሰፊው ተንቀሳቅሷል፡፡ የታክስ ማሻሻያ ፕሮግራሙ የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ አካል በመሆን የታክስ ፖሊሲውንና አስተዳደሩን ለማደስ የሚያስችሉ የማሻሻያ አሠራሮችን በሚከተሉት ዙሪያ ተግባራዊ አድርጓል፡፡

- የታክስ ህግ፣ ደንብና መመሪያዎችን ማሻሻልና ሥራ ላይ ማዋል

- የታክስ ከፋዮች ምዝገባ

- የቁርጥ ግብር አሰራር (Presumptive Taxation)

- የተጨማሪ እሴት ታክስ ሥራ ላይ ማዋል

- የታክስ አስተዳደሩን ቀልጣፋ ውጤታማና ዘመናዊ ማድረግ

- የታክስ ከፋይ ትምህርትና ቅስቀሳ

እነዚህና ሌሎች የታክስ ፖሊሲና አስተዳደር ማሻሻያዎች በአገር ዓቀፍ ደረጃ ተግባራዊ የተደረጉ ሲሆን፣ ለቀልጣፋ አፈጻጸማቸውም የፌዴራልና የክልል ገቢ ሰብሳቢ ክፍሎች በጋራና በምክክር እንዲሠሩ የተደረገ ሲሆን በአፈፃፀሙም ግብር ከፋዮ ቀጥተኛ ተሳትፎ እንዲኖረው ተደርጓል፡፡ በጥቅሉ የተወሰዱት የታክስ ማሻሻያ እርምጃዎች የታክስ ፖሊሲውን ገቢን ከማመንጨት ባሻገር የዜጐችን የመሥራት ፍላጐት እንዳይጫን፣ የአገር ውስጥና የውጭ ኢንቨስትመንትን በዓይነትና በብዛት ለመሳብ እንዲሁም ክልላዊ ሥርጭትን ለማስተካከል፣ የታክስ መሠረቱን በማስፋት፣ አስተዳደሩን ቀልጣፋና ውጤታማ በማድረግ፣ የታክስ ስወራና ማጭበርበርን በመቀነስ በራስ ተነሳሽነትን በማጐልበት ገቢን የማሳደግ ዓላማን ያነገቡ ናቸው፡፡

ስለሆነም የተወሰዱት የታክስ ፖሊሲ፣ አስተዳደራዊና ተቋማዊ ማሻሻያዎች ከ1994 ወዲህ የታክስ ገቢው ከፍተኛ ዕድገት እንዲያሳይ ረድተዋል፡፡ በዚህ ሁኔታም በ2008 በጀትዓመት በፌዴራልና በክልሎች የተሰበሰበው ጠቅላላ የታክስ ገቢ ብር196 ቢሊዮን የደረሰ ሲሆን በ1994 መጠኑ ብር 7.8 ቢሊዮን እንደነበር ይታወሳል፡፡ የታክስ አሰባሰቡ ባለፉት 15 ዓመታት በአማካይ 21 በመቶ ዕድገት አሳይቷል፡፡

## 4.2. የመንግሥት ወጪ አመዳደብና አስተዳደር

ባለፉት በርካታ ዓመታት ሥራ ላይ የዋለው የፊሲካል ፖሊሲ የመንግሥት ገቢ ለማሳደግ ትኩረት ከመሰጠቱም ባሻገር የተሰበሰበው ገቢ የመንግሥትን ኃላፊነት ለመወጣት በሚያስችሉ ልማትን ለማፋጠንና፣ ድህነትን ለመቀነስና መሠረታዊ አገልግሎቶችን ለማቅረብ በሚረዱ የወጪ ዘርፎች የተመደበና አስተዳደሩም ውጤታማ እንዲሆን በርካታ የማሻሻያ እርምጃዎች ተቀርጸው ተግባራዊ ሆነዋል፡፡

## 4.3. የልማትና የድህነት ቅነሳ ፖሊሲና ስትራቴጂ

ከ1984-1993 በነበሩት 10 ዓመታት የሽግግሩ ወቅት መንግሥት ሆነ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግሥት አገሪቱን ከድህነት ለማውጣት የሚያስችል መሠታዊ የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራሞች ተነድፈዋል፡፡ ፕሮግራሞቹን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ እስትራቴጂዎችና ስልቶች የተዘረጉ ሲሆን ዋና ዋና የኢኮኖሚና ማህበራዊ ክፍላተ ኢኮኖሚዎች የሚመሩበት ፕሮግራሞችንም ሥራ ላይ ውለዋል፡፡ ሆኖም እነዚህ እንቅስቃሴዎች ፈጣንና ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚና ማህበራዊ ለውጦችን ማምጣት ባለመቻላቸው መንግስት በ1994 ዓ.ም ወዲህ የኢኮኖሚ ፖሊሲውን በማሻሻልከድህነት በአጭር ጊዜ ለመላቀቅና የኢኮኖሚ ልማትን ለማፋጠን የልማታዊ መንግስት ሞዴል ተመራጭ ሆኗል፡፡የኢኮኖሚ ፖሊሲን ከልማታዊ መንግስት ሞዴል ጋር በማጣጣም ልዩ ልዩ የክፍላተ ኢኮኖሚ ፖሊሲ፣ እስትራቴጂና ስልቶችን በመንደፍ ተግባራዊ ሆነዋል፡፡ ከእነዚህ መካከል ሚከተሉት በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡ እነዚህም፡-

- የገጠር ልማት ፖሊሲ፣ እስትራቴጂ እና ስልቶች፣
- የኢንዱስትሪ ልማት እስትራቴጂ፣
- የማስፈፀም አቅም ግንባታ እስትራቴጂና
- በኢትዮጵያ የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ናቸው፡፡

በእነዚህ የመንግሥት ፖሊሲ፣ እስትራቴጂና ፕሮግራሞች ላይ መሠረታዊ ጽሁፎች እንዲዘጋጁ፣ ለዜጐች እንዲሠራጩና በውይይት እንዲዳብሩ ተደርጓል፡፡ ይህም አካሄድ በአገሪቱ የልማት እስትራቴጂ ስልትና አፈጻጸም ላይ አስፈጻሚ አካላትና ህዝቡ በቂ ዕውቀትና ግንዛቤ እንዲኖራቸው እንዲሁም አገራዊ የጋራ አመለካከትና እምነት እንዲኖር ለማድረግ ረድቷል፡፡

እነዚህን መሠረታዊ የመንግሥት ፖሊሲና እስትራቴጂዎች መሠረት በማድረግ ከ1995 ጀምሮ ተከታታይነት ያላቸው የድህነት ቅነሳ ፕሮግራሞች ሥራ ላይ ውለዋል፡፡ የመጀመሪያው የዘላቂ ልማትና የድህነት ቅነሳ ፕሮግራም (SDPRP) ከ1995-1997 ተግባራዊ የተደረገ ሲሆን፣ በቀጣይም በዚህ ፕሮግራም የአፈጻጸም ግምገማ ላይ በመንተራስ ከ1998-2002 የቆየ ሁለተኛው ፈጣንና

ቀጣይነት ያለው ልማት በማስፈን ድህነትን በሂደት ማስወገድ ዓላማው ያደረገ (PASDEP) የልማት ዕቅድ ተዘጋጅቷል፡፡ በአሁኑ ወቅት በመተግበር ላይ ያሉት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዶች፤ (GTP) ከ2003-2007፣ እንዲሁም (GTP) IIከ2008-2012 በመካሄድ ላይ ይካሄዳል፡፡

የተጠቀሱት የልማትና ድህነት ቅነሣ ብሎም አገሪቱን ከድህነት ለማላቀቅ እንደሚረዱ የታመነባቸው ፕሮግራሞች ከቀበሌ እስከ አገር አቀፍ ህብረተሰቡን እንዲሁም የአገሪቱን የልማት አጋሮች በማሳተፍ የተዘጋጁ ናቸው፡፡ እያንዳንዱ የልማት ዕቅድም አገራዊና ዓለም አቀፍ ነባራዊ ሁኔታዎችን እንዲሁም ወቅታዊ የአገሪቱን ሁኔታ በማገናዘብ የየራሳቸውን መሠረታዊ የትኩረት አቅጣጫዎች ያስቀምጣሉ፡፡

የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዶች ፈጣን ዕድገትን ከማስገኘት ባሻገር በሁሉም ዘርፎች የተሻለ ውጤትን በማስመዝገብ አገሪቱን ከድህነት በማላቀቅ በሚቀጥሉት 10-15 ዓመታት ወደ መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ለማሰለፍ የሚያስችሉ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ዕድገት መሠረቶችን ለመገንባት ዓላማ ያደረጉ የልማት ምሶሶዎችን ቀምሯል፡፡ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በሚል ርዕስ የተዘጋጀው የ5 ዓመቱ የልማት ዕቅድ ዓበይት ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡ እነዚህም፡-

- ቢያንስ 11 በመቶ ዓመታዊ አማካይ የአጠቃላይ ምርት ዕድገት በማስመዝገብ የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች ማሳካት፣
- የትምህርትና ጤና አገልግሎቶችን ተደራሽነትና ጥራት በማረጋገጥ የማህበራዊ ዘርፉን የምዕተ ዓመቱን ግቦች ማሳካት፣
- የተረጋጋ ዲሞክራሲያዊና ልማታዊ መንግሥት በመፍጠር ለዘላቂ አገራዊ ልማት አመች ሁኔታ መፍጠር፣ እና
- በተረጋጋ የማክሮኢኮኖሚ ማዕቀፍ ከፍ ብለው የተጠቀሱትን ዓላማዎች በማሳካት ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገትን ማረጋገጥ የሚሉት ናቸው፡፡

እነዚህን ዓላማዎች በማሳካት ፈጣን፣ ቀጣይና ሁሉን አቀፍ የሆነ የኢኮኖሚ ዕድገት ለማምጣት የሚያስችሉ እስትራቴጂዎች በዕቅዱ ተካተዋል፡፡ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድም ሆነ ያለፉት የዘላቂ ልማትና ድህነት ቅነሣ ፕሮግራሞች አመርቂ ውጤት ማሳየታቸውን በየጊዜው የተደረጉ የአፈጻጸም ግምገማዎችና ሪፓርቶች አሳይተዋል፡፡

## 4.4. ድህነት ተኮር ወጪዎች

አገራችን ዘርፈ ብዙ የልማት እንቅስቃሴ በማድረግ የዜጐችን የኢኮኖሚና ማህበራዊ ህይወት ለማሻሻል በድህነት ላይ ጦርነት መክፈቷ ይታወቃል፡፡ ለዚህ ዓላማ መሳካትም መንግሥት አግባብ ያለው ፖሊሲን ከመቅረፅና ለግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ አመች ሁኔታን ከመፍጠር ባሻገር ድህነት ተኮር

በሆነ የልማት ተግባሮች ላይ በሰፊው በመሳተፍ ላይ ይገኛል፡፡ በዚህ ረገድ አብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል የተሰማራበት የግብርናና ገጠር ልማት እንዲሁም የምግብ ዋስትና ማስጠበቅ ተግባራት ግምባር ቀደም ናቸው፡፡ የኢኮኖሚ ዕድገትን ከማምጣት ባሻገር የህብረተሰቡን ማህበራዊ ኑሮ ለማሻሻል ለሚደረጉ የትምህርት፣ ጤናና ውሃ መሰል አገልግሎቶችን ማስፋፋት እና ለመንገድ ግንባታ ትኩረት በመስጠቱ ለእነዚህ ዘርፎች የዋለው ወጪ ከጠቅላላው የመንግሥት ወጪ ከፍተኛ ድርሻ መያዙን መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

መንግሥት ለድህነት ተኮር ወጪዎች የሰጠው ትኩረት ቀደም ካሉት ዓመታት ጀምሮ ቢሆንም ዕድገቱ ከ1994 ወዲህ የሰፋ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ለእነዚህ የወጪ ዘርፎች የዋለው ወጪ በ2008 ዓ.ም 70 በመቶ በመድረስ በ1994 ከነበረው በእጥፍ አድጓል፡፡ በዚህም የዜጐችን ገቢ ከማሳደግና መሠረታዊ አገልግሎትን ከማስፋፋት ጋር የተያያዙት የግብርናና ገጠር ልማት፣ መንገድ፣ ትምህርት፣ ጤና እና ውሀ አቅርቦት ወጪዎች ከፍተኛ መጠን ከፋ ብሏል፡፡ ይህም በሌሎች የአፍሪካ አገሮች ከሚታየው ከ35 በመቶ ያልበለጠ የወጪ ድርሻ ከእጥፍ በላይ ሆኗል፡ ፡ እዚህም ላይ በ1980ዎቹ መጀመሪያ የነበረው የአገራችን የተጠቀሱት ዘርፎች ወጪ ከወቅቱ የአፍሪካ አገራት አፈፃፀም ጋር ተቀራራቢ እንደ ነበር ማስታወስ ይቻላል፡፡ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ትኩረት የተሰጣቸውና ድህነትን በከተማ የመቀነስ ዓላማ ያላቸው የመኖሪያ ቤቶችና የአነስተኛ እና ጥቃቅን ኢንዱስትሪዎች ልማት ወጪ በዚህ መረጃ ቢካተቱ የድህነት ተኮር ወጪው ድርሻ ከዚህም በላይ ሊሆን እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል፡፡

## 4.5. የመንግሥት ወጪን ውጤታማ ማድረግ

ከ1994 ወዲህ የወጪ አስተዳደሩ የፋይናንስ ዲሲፕሊን የሚያጐለብት ቀልጣፋና ዘመናዊ በሆነ ሥርዓት እንዲመራ ለማድረግ የሚያስችሉ የአሠራር ማሻሻያዎች ተግባራዊ ሆነዋል፡፡ ይህንንም ለማስፈፀም የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ አካል የሆነ የመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ንዑስ ፕሮግራም ተደራጅቶ የመንግሥት ፋይናንስ አስተዳደር በህግ እንዲመራ፣ በዘርፉ የሰለጠነ የሰው ኃይል በማፍራት፣ ዘመናዊ፣ ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ለኢኮኖሚ ዕድገት አጋዥ የሆነ የህግ ተጠያቂነትን የሚያሰፍን የፋይናንስ አስተዳደርና ቁጥጥር ሥርዓትን በመዘርጋት በርካታ ውጤቶችን ያስመዘገበ ሲሆን፣ አፈጻጸሙም በቀደመው ምዕራፍ /በተራ ቁጥር 3 ስር/ በዝርዝር ቀርቧል፡፡

የአገራችን የልማታዊ መንግስት በጀት አመዳደብን ስንመለከትም ከመደበኛ ወጪዎች ይልቅ ለልማት ትኩረት ማድረጉን ካለፉት ዓመታት የበጀት መረጃ መረዳት እንችላለን፡፡ ለማነጻር ያህልም የበጀት አመዳደቡ በ1983 በጀት ዓመት የካፒታል ወጪ የጠቅላላ ወጪውን ሩብ ያህል የነበረ ሲሆን፣ በ1984 ድርሻው ወደ 35 በመቶ ከፍ ብሏል፡፡ በሂደት ደግሞ የካፒታል ወጪው ድርሻ እያደገ መጥቶ ላለፉት በርካታ አመታት ወደ 60 በመቶ ሊያድግ ችሏል፡፡ ይህም

ለኢንቨስትመንት የሚመደበው በጀት ድርሻ ከአብዛኛዎቹ የአፍሪካ አገሮች አማካይ ድርሻ ጋር ሲነጻጸር እጅግ የላቀ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለውም የአገራችን በጀት ድልድል ዕለታዊ ፍጆታን ከመሸፈን ይልቅ ቁሳዊ ሀብትን ለሚያፈሩ የልማት ሥራዎች ትኩረት መስጠቱንና የወጪ አስተዳደሩን ውጤታማነት ያመለክታል፡፡

## 4.6. ያልተማከለ የፋይናንስ አስተዳደር (Deepen Fiscal Decentraliztion)

አገራችን የምትከተለውን የፌዴራላዊ መንግሥት አወቃቀር ለመተግበር የተዘረጋው ያልተማከለ የፋይናንስ ሥርዓት ባለፉት 10 ዓመታት ይበልጥ ተጠናክሮ ቀጥሏል፡፡ በመሆኑም የፌዴራል መንግሥትም ሆነብሄራዊ ክልላዊ መንግሥታት በህገ መንግሥቱ ተለይቶ በተሰጣቸው የገቢ እና ወጪ ክፍፍል መሠረት ገቢን ሰብስበው ወጪዎችን በመሸፈን መሠረታዊ አገልግሎቶችን ለህብረተሰቡ በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡ ሆኖም ለብሄራዊ ክልላዊ መንግሥታት የተሰጡ የገቢ መሠረቶችና የወጪ ኃላፊነቶች የሚጣጣሙ ባለመሆኑ ከፌዴራል መንግሥት የበጀት ድጋፍ ይደረጋል፡፡ የመንግሥት የወጪ ትኩረት የሆኑ የኢኮኖሚ ዕድገትና የድህነት ቅነሳ የልማት ተግባራት የሚከናወኑት በአመዛኙ በክልሎች በመሆኑ የበጀት ድጋፉን በየጊዜው ማሳደግ ግዴታ ሆኗል፡፡ በዚህ ሁኔታም በ1993 ለብሄራዊ ክልላዊ መንግሥታት የተላከው የበጀት ድጋፍ ብር 3.5 ቢሊዮን ሲሆን በ2009 መጠኑ ወደ ብር 108.6 ቢሊዮን አድጓል፡፡

እያደገ የመጣው የበጀት ድጋፍ ያልተማከለ የፋይናንስ ሥርዓቱን በማጠንከር የክልሎችንና የወረዳ አስተዳደሩን ራስን በራስ የማስተዳደር ብቃት እና አገልግሎት አሰጣጥ በማጐልበት፣ በፌዴራልና በክልሎች እንዲሁም በተለያዩ ክልሎች መካከል ያለ የገቢና የዕድገት ልዩነት በማጥበብ፣ እንዲሁም የፋይናንስ ሀብትን አመዳደብ ውጤታማ በማድረግ፣ የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ ማኔጅመንት ለመፍጠር ያደረገው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው፡፡

# 5. ውስጣዊ እና ውጫዊ ሁኔታዎች ትንተና

የመንግሥት ፋይናንስ አስተዳደር የማሻሻያ ሥራዎች አፈጻጸም በመገምገም ጎልተው የታዩ የውስጥና የውጭ አካባቢ ትንተና (ጥንካሬዎች፣ ድክመቶች፣ መልካም አጋጣሚዎችና ሥጋቶች) ከዚህ በታች ቀርቧል፡፡

## 5.1. ውስጣዊ ሁኔታ

### 5.1.1. ጥንካሬዎች

- የመንግሥት ፋይናንስ አስተዳደር የሚመሩባቸው የተሟሉና ወጥነት ያላቸው የፋይናንስ፣ ግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጆች፣ ደንብ፣ መመሪያዎች፣ ማንዋሎች ተዘጋጅተው ሥራ ላይ መዋላቸው፣

- የማክሮ ኢኮኖሚና ፊስካል ማዕቀፍ /MEFF/ በመዘጋጀቱ የበጀት ዝግጅት ከአጭር ጊዜ ዕይታ ወጥቶ ወደ መካከለኛ ዘመን ዕይታ መሸጋገሩ፣
- በክልሎች ደረጃ የበጀት አሰራሩ ቀድሞ ከነበረበት የዜሮ በጀት አሰራር ሙሉ በሙሉ ወጥቶ በወጪ አርዕስት ወደ ተመሰረተ የበጀት አሰራር /Line item bugetting/ መቀየሩ፣
- በፌዴራል ደረጃ የበጀት አሰራሩ ከወጪ አርዕስት አሰራር ወጥቶ በውጤት ላይ ወደ ተመሰረተ የፕሮግራም በጀት መሸጋገሩ፣
- በፌዴራልና ክልል ደረጃ የመንግስት የጥሬ ገንዘብ ዕቅድ እየተዘጋጀ ክፍያዎች በዕቅድና በዜሮ ሚዛን የክፍያ ዘዴ መፈጸማቸው፣
- የመንግሥት ሂሣብ ምዝገባ ሥርዓት ከነጠላ ሂሳብ ወደ ጥሬ ገንዘብ ላይ የተመሠረተ የተሻሻለ የጣምራ ሂሣብ አያያዝ ሥርዓት ተቀይሮ በፌዴራልና ክልል ደረጃ ተግባራዊ መደረጉ፣
- እያንዳንዱ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሂሣቡን ዘግቶ የሚያቀርብበት፣ የሚያስመረምርበትና የሚጠየቅበት ሥርዓት “Self Accounting and Reporting” ተዘርግቶ በፌዴራልና ክልል ደረጃ ተግባራዊ መደረጉ፣
- የውስጥ ኦዲት አሰራር ከቅድመ ኦዲት ወደ ድህረ ኦዲት ተለውጦ በፌዴራልና ክልል ደረጃ ተግባራዊ መደረጉ፣
- በፌዴራል ደረጃ የውስጥ ኦዲት ተጠሪነት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በማድረግ ሙያዊ ነፃነታቸው እንዲጠበቅ መደረጉ፣
- የኦዲት ኮሚቴ አሰራር በወረዳ ደረጃ ተግባራዊ መደረጉ፣
- የመንግስት ግዥ መንግስት ሊያገኝ የሚገባውን ጥቅም ባስጠበቀ /value for money/ መልኩ፤ አሳታፊ፣ ግልጽ እና ተጠያቂነት በሰፈነበት ሁኔታ እንዲፈጸም የሚያስችል ስርዓት ተዘርግቶ በፌዴራልና በክልሎች ተግባራዊ መደረጉ፣
- የስትራቴጂክ እቃዎች ግዥ በማዕቀፍ የሚከናወንበት ስርዓት መዘርጋቱ፣
- የመንግስት ቋሚና አላቂ ንብረት የሚመዘገብበት፣ የሚተዳደርበትና አገልግሎታቸው ሲያበቃ የሚወገዱበት ስርዓት ተዘርግቶ በፌዴራልና በክልሎች ተግባራዊ መደረጉ፣
- የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር ስራዎችን በቴክኖሎጂ ለመደገፍ የተቀናጀ የበጀትና የሂሳብ መረጃ ሥርዓት (IBEX) ለምቶ በፌዴራል፣ የክልል ሴክተር መስሪያ ቤቶች፣ በዞንና ወረዳ የገ/ኢ/ል/ጽ/ቤቶች ተግባራዊ መደረጉ፣

- የተቀናጀ የመንግሥት ፋይናንስ መረጃ ሥርዓት (IFMIS) በ32 የፌዴራል ባለበጀት መስሪያ ቤቶች ተግባራዊ መደረጉ፣
- ልዩ ልዩ የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም የመንግስት ፋይናንስ መረጃዎች ለዜጎች እንዲደርስ፣ ሥልጠና በመስጠት እና በቅድመ በጀት ውይይቶች ላይ እንዲሳተፉ በማድረግ የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት አሰራር በሁሉም የአገሪቱ ወረዳዎች መተግበሩ፣
- በመንግሥት ፋይናንስ አስተዳደር ላይ የባለሙያውንና የኃላፊዎችን አቅም ለማጎልበት የሥልጠና ሞጁሎችን በማዘጋጀት በተከታታይ ለበርካታ ዓመታት ሥልጠና መሰጠቱ፣
- በመንግሥት ፋይናንስ አስተዳደር ላይ የሚሰሩ ባለሙያውንና ኃላፊዎችን የሙያ ደረጃ ለማሳደግ በተቀናጀ መልኩ ተቀማዊ ስልጠና መሰጠት መጀመሩ፣

## 5.1.2. ድክመት

- በመንግሥት ፋይናንስ፣ ግዥና ንብረት አስተዳደር ውስጥ የሚታዩትን ኪራይ ሰብሳቢነት ለማስቀረት አለመቻሉ፣
- የመንግሥት ፋይናንስ፣ ግዥና ንብረት አስተዳደር ስራዎች በወጡት አዋጆች፣ ደንብና መመሪያዎች መሠረት ተሟልተው አለመተግበራቸው፣
- በመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር ላይ በእውቀት፣በክህሎት እና በአመለካከት የዳበረ በቂ ልምድ ያለው ባለሙያ አለመኖሩ፣
- በፌዴራልም ሆነ በክልሎች ለፊሲካል ፖሊሲ ጥናቶችና ግምገማዎች የሚስፈልጉ መረጃዎች አያያዝ ደካማ መሆኑ፤
- የፕሮግራም በጀት አሠራር በክልሎች አለመተግበሩ፣
- ከፌዴራል መስሪያ ቤቶች ጋር የፕሮግራም በጀት የውል ስምምነት /Performance Agreement/ ስለማይደረግ ተጠያቂነትን ማስፈን አለመቻሉ፣
- የፕሮግራም በጀት ዝግጅትና ወጪትን ከጀት ጋር አስተሳስሮ በመገምገም ረገድ ከፍተኛ ክፍተት መኖሩ፣
- የፋይናንስ መረጃ ያልሆኑ የፕሮግራም በጀት ዓላማዎች፣ ውጤቶች፣ የውጤት አመላካቾች፣ ግቦች እና የፕሮጀክት መግለጫ ዝግጅት በመረጃ ቴክኖሎጂ ታግዘው አለመዘጋጀታቸው፣
- የፕሮግራም በጀት የአሰራር ሂደት በአግባቡ የስርዓተ ፆታን ጉዳይ አለማካተቱ፣
- የፕሮጀክቶች መረጃ አያያዝ፣ ክትትልና ግምገማ ደካማ በመሆኑ ምክንያት በታቀደው

ጊዜ፣ወጪና ጥራት አለመጠናቀቃቸው፣

- የጥሬ ገንዘብ ዕቅዶችን፣መርሃ ግብሮችን፣ የአፈጻጸም ሪፖርቶችን፣ የጥሬ ገንዘብ ፍላጎትን፣የሂሳብ እና የኦዲት ግኝት ማስተካከያዎችን በወቅቱንና በጥራት በባለበጀት መ/ቤቶች በኩል ተዘጋጅቶ እንዲቀርብ የክትትልና ድጋፍ ስራዎች በቂ አለመሆን ፣
- የውስጥ ኦዲት አሰራር በመረጃ ቴክኖሎጂ አለመደገፍ እና ሥጋትን መሰረት ያደረገ የኦዲት አሰራር አለመተግበር፣
- የተቀናጀ የመንግሥት ፋይናንስ መረጃ ሥርዓት (IFMIS) ትግበራ አዝጋሚ መሆኑ እና ከስርዓቱ ጋር ለተገኛኙ ችግሮች ፈጣን ምላሽ አለመስጠት፣
- የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የፋይናንስ አስተዳደር አደረጃጀት የተዘበራረቀ በመሆኑ ምክንያት በባለሙያው ተረጋግቶ መሰራት ላይ ተጽዕኖ መፍጠሩ፣
- በመንግስት ወጪ አስተዳደር እና ቁጥጥር ማሻሻያ ፕሮግራም እስከአሁን የተደረጉ የማሻሻያ ስራዎች ያመጡት ለውጥ በገለልተኛ አካል አለመገምገሙ፣
- ከመንግስትና ከህዝብ ክንፍ ጋር ሳይቆራረጥ ውይይቶች አለማድረግና አብሮ አለመስራት፣

## 5.2. ውጫዊ ሁኔታ ዳሰሳ

በአገሪቷ የተነደፈውን የልማት ፕሮግራም ፋይናንስ ለማድረግ እና የተሰበሰበው ሀብት በሕጉና በመመሪያውመሠረትሥራላይለማዋልውጫዊ(ፖለቲካዊ፣ኢኮኖሚያዊ፣ማህበራዊ፣የቴክኖሎጂ እና የህግ ሁኔታዎች) ዳሰሳ በማድረግ የሚከተሉት መልካም አጋጣሚዎች እና ሥጋቶች ተለይተዋል፡፡

### 5.2.1. መልካም አጋጣሚዎች

- በአገር አቀፍ ደረጃ የዲሞክራሲና የመልካም አስተዳደር ግንባታዎች ትኩረት ተሰጥቶአቸው ይበልጥ ስር እንዲሰዱና እንዲጠናከሩ መንግስት ቁርጠኛ አቋም ወስዶ መንቀሳቀሱ፣
- በአገሪቱ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት እየተስፋፉ በመምጣታቸው ብዛት ያላቸው ዜጎች በመንግስተ ፋይናንስ አስተዳደር የትምህርት መስኮች ተመርቀው የሰው ሃይል ክፍተቱን ለመሙላት ምቹ ሁኔታ መፈጠሩ፣
- የአገልግሎት አሰጣጡን ውጤታማ ለማድረግ በሀገር አቀፍ ደረጃ የተለያዩ የለውጥ ሥራዎች ማለትም የመሠረታዊ የአሠራር ሂደት ለውጥ፣ ሚዛናዊ የውጤት ተኮር ሥርዓት፣ የዜጎች ቻርተርና የለውጥ ሠራዊት ግንባታ ስትራቴጂ ተነድፈው ስራ ላይ መዋላቸው፣

- ሀገራዊና የተቋም ራዕይ መቀረፆ ወደ ስራ በመገባቱ ተነሳሽነትን መፍጠሩ፣
- ያልተማከለ የመንግሥት ፋይናንስ አስተዳደር ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉ፣
- በኢኮኖሚ ዕድገቱ ምክንያት የመንግሥት ገቢ በየዓመቱ ከ25% በላይ በማደጉ የመንግሥት ወጪ አስተዳደር ማሻሻያን ፋይናንስ ለማድረግ ጥሩ አጋጣሚ መፍጠሩ፣
- የመንግስትን የበጀት ጉድለት ከመሙላት አንፃር ከልማት አጋሮች ጋር ያለው ግንኙነት እየተጠናከረ በመምጣቱ ከጊዜ ወደጊዜ የግኝትና ፍሰት መጠን መጨመሩ፣
- የድህነት ቅነሳ ላይ ያተኮሩ የትምህርት፣ የጤና፣ የውሃ፣ የኤሌክትሪክና ሌሎች የመሰረተ ልማት ፖሊሲዎች ተቀፀርው ሥራ ላይ መዋላቸው፣
- በዓለም ላይ የመረጃ ስርዓት ቴክኖሎጂ በፍጥነት እያደገ መምጣቱ፣
- በአገሪቱ የህዝብ ሃብት ፍትሃዊ ክፍፍል እና ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ ህገመንግስት እና ፖሊሲዎች፣ስትራቴጂዎች እንዲሁም ሌሎች የህግ ማዕቀፎች መኖራቸው፣

## 5.2.2. ሥጋቶች

- ቀጠናዊ እና አለማቀፋዊ የፖለቲካ አለመረጋጋት
- የተቋማት ስትራቴጅውን ማስፈጸም አቅም ውስንነት እና የባለሙያ ፍልሰት መኖር
- የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደሩን በመረጃ ስርዓት ለመደገፍ የሚዘረጉ የመሰረተ ልማቶች በበቂ መጠን እና ጥራት አለመዘርጋት
- መንግስት ያቀዳቸውን የልማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ለማስፈፀም የሚጠበቀው የገቢ መጠንና ወጪ ያልተጣጣመ መሆን
- ያልታሰቡ የተፈጥሮዓዊ አደጋዎች መከሰት

## 5.2.3. አስቻይና ፈታኝ ሁኔታዎች

### ሀ/ አስቻይ ሁኔታዎች

- አገራችን በምትከተለው ፖሊስ ምክንያት የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂና የንግድ ባንኮች የተስፋፉ ስለሆነ እና የመንግሥት ፋይናንስ አስተዳደሩም የእነዚህን የፋይናንስ ተቋማት መሰረተ ልማቶች የሚጠቀም በመሆኑ የዘርፉን ስራ ጥራትና ቅልጣና ለመጨመር የጎላ አስተዋጽኦ አላቸው፡፡

- በአለፉት ጊዜያት የተለያዩ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች የመንግሥት ፋይናንስ ግዥ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መውጣታቸው እና ሥራ ላይ መዋላቸው ይህን እስትራቴጂ ሥራ ላይ ለማዋል ይረዳል፡፡
- የመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ማሻሻያ ፕሮግራሞችን በመምራት የተወሰነ ልምድ በመኖሩ አዲሱን እስትራቴጂ ሥራ ላይ ለማዋል ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡

### ለ/ ፈታኝ ሁኔታዎች

- በፋይናንስ ዘርፉ በሚደረጉ ማሻሻዎችን ተከተሎ የሚዘረጉ አዳዲስ አሰራሮችንና ቴክኖሎጂዎችን ተቀብሎ ለመተግበር የሠለጠነ የሰው ኃይል በበቂ ቁጥርና ብቃት በማዘጋጀት ላይ የሚታይ ክፍተት፣
- የመ/ቤት የበላይ ኃላፊዎች ለመንግሥት ፋይናንስ አስተዳደር የሚሰጡት ትኩረት አነስተኛ መሆኑ ናቸው፡፡

## 6. የስትራቴጂው የትኩረት መስኮችና ግቦች

ስትራቴጂውን ለማስፈጸም ዘጠኝ ግቦች የተቀረጹ ሲሆን እነዚህም የመንግሥት ፋይናንስ አስተዳደር ግልጽነት፣ ተጠያቂነት፣ ውጤታማነት፣ ፍትሃዊነት፣ ዘመናዊነትን እና የአገልግሎት አሰጣጥን ያሻሽላሉ፡፡ ይህ እስትራቴጂ በዋናነት ትኩረት የሚሰጠው በአለፉት ዓመታት ተሠርተው ሥራ ላይ የዋሉትን የማሻሻያ ሥራዎችን የማጠናከርና ከኢኮኖሚ ዕድገቱ ጋር አብሮ ሊሄድ የሚችል አዳዲስ የሪፎርም ፕሮግራሞችን ለመተግበር ነው፡፡

በዚህ ስትራቴጂክ እቅድ ሰነድ የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት፣ የኢትዮጵያ ሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ ጽ/ቤት እና ሌሎች ከገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ውጪ የሚገኙ የተቆጣጣሪ አካላት የማሻሻያ ተግባራት በራሳቸው ስልጣንና ተግባር እናዲሁም ስትራቴጂ የሚመሩ በመሆናቸው እነዚህን የሚመለከቱ ተግባራት አልተካተቱም፡፡

በዚህ ስትራቴጂ የተቀረጹ ግቦች ፊስካል ፖሊሲ፣ በፕሮግራም በጀት፣ በጥሬ ገንዘብ ዕቅድ፣ በክፍያ አሰራር፣ብድር አስተዳደር፣ በግዥ እና ንብረት አስተዳደር አፈጻጸም፣ መንግሥት ሂሣብ ሪፖርትና በኦዲት አፈጻጸም በኩል የታዩትን ተግዳሮቶችና ችግሮች የሚፈቱ እንዲሁም የመንግስት ፋይናንስ ስርዓቱን ወደላቀ ደረጃ የሚያሸጋግሩ ናቸው፡፡ እያንዳንዱ ግብ ለማስፈጸም የሚከናወኑ ተግባራቶች እና የሚገኘውን ውጤቶችን የያዘ ነው፡፡ የግቦቹ ውጤት ለመገኘታቸው የውጤት አመልካቾችና መለኪያዎች ተቀምጧል፡፡ በዚህም መሠረት የትኩረት መስኮቹና ግቦቹ በዝርዝር ከዚህ በታች ቀርበዋል፡፡

## ግብ-1 የመንግስት ገቢና ወጪ እንዲጣጣም ማድረግ፣

ተግባር 1፡- የፊሲካል ፖሊሲ አቅም በማጎልበት የማክሮ ኢኮኖሚና ፊሲካል ማዕቀፍ /MEFF/ ሠነድ ጥራትን ማሻሻል፣

ተግባር 2፡- ዋና ዋና የፊስካል ስጋትን (Fiscal Risk) በመለየትና በመተንተን የመፍትሔ አቅጣጫዎችን ማስቀመጥ፣

ተግባር 3፡- የመንግሥት ገቢና ወጪ አፈጻጸም መረጃዎች የማሰባሰብ፣ የማጠናቀርና የመተንተን አቅምን ማጠናከር፣

ተግባር 4፡- የታክስ ፖሊሲ ሰነዶች ጥራት ለማሻሻል የባለሙያዎችን አቅም በስልጠና መገንባት፣

ተግባር 5፡- የኢትዮጵያን ጥቅም ያስጠበቁ የተደራራቢ ታክስ ስምምነቶች ማድረግና አፈፃፀማቸውን መከታተል፤ የተደራራቢ ታክስ ስምምነት የሚፈፀምበት ቀመር /ሞዴል/ ማሻሻል፤

ተግባር 6፡- የአገሪቱን የታክስ ገቢ መሰረት ለማስፋት እና ለማሳደግ ጥናቶችንና ግምገማዎችን በማካሄድ አዳዲስ የታክስ ፖሊሲዎችን መቅረፅ፣

ተግባር 7፡- የመንግስትንና የግል ዘርፍ አጋርነት የሚመሩባቸው መመሪያዎች እና ዝርዝር የአሰራር ሰነዶች /Guildelines/ ማዘጋጀት፣

ተግባር 8፡- በመንግስትና የግሉ ዘርፍ አጋርነት የሚቀርቡ ፕሮጀክቶች ቅድመና ድህረ የአዋጭነት ጥናት ግምገማ፣ የፕሮጀክቶች ቅድመ ፍላጎት፣ የፍላጎት፣ የግምገማና የማጽደቅ ስርዓቶች የሚመሩባቸው ሠነዶችን ማዘጋጀት፣

ተግባር 9፡- የመንግስትና የግሉ ዘርፍ አጋርነት ስራ አመራር፣ ቦርድ፣ የኮንትራት ባለስልጣን እና የፕሮጀክት አስተዳደር ቡድኖች አደረጃጀት፣ ተግባርና ኃላፊነት የሚገልጽ አደረጃጀትን ማጥናትና መተግበር፣አቅም መገንባት፣

## የሚጠበቅ ውጤት

ውጤት 1፡- በጥራት የተዘጋጀ የማክሮ ኢኮኖሚና ፊሲካል ማዕቀፍ /MEFF/፣

ውጤት 2፡- ተተንትኖ የመፍትሔ አቅጣጫዎች የተቀመጡለት ዋና ዋና የፊስካል ስጋቶች፣

ውጤት 3፡- የተሟላና ደረጃቸውን የጠበቁ የመንግሥት ገቢና ወጪ አፈጻጸም መረጃዎች፣

ውጤት 4፡- በጥራት የተሻሻሉ የታክስ ፖሊሲ ሰነዶች፣

ውጤት 5፡- የተፈረሙ ስምምነቶችና የተሻሻለ የተደራራቢ ታክስ ስምምነት ቀመር/ሞዴል/፤

ውጤት 6፡- ያደገ የታክስ ገቢ፣

ውጤት 7፡- የተዘጋጁ የመንግስትንና የግል ዘርፍ አጋርነት የሚመሩባቸው መመሪያዎች እና የአሰራር ሰነዶች፣

ውጤት 8፡- የተዘጋጁ የፕሮጀክት ግምገማ ሰነዶች፣

ውጤት 9፡- የተዘጋጁ የመንግስትና የግሉ ዘርፍ አጋርነት ስራ አመራር፣ ቦርድ፣ የኮንትራት ባለስልጣን እና የፕሮጀክት አስተዳደር ቡድኖች አደረጃጀት ሠነድ፣

## ግብ-2 የበጀት አመዳደብና አጠቃቀም ወጪ ቆጣቢ እና ውጤታማ ማድረግ፣

ተግባር 1፡- በጀትን ከውጤት ጋር በማስተሳሰር ረገድ የፕሮግራም በጀት አፈጻጸም ያለበትን ድክመት በማጥናት ክፍተቶችንና ችግሮችን መለየት፣ የማሻሻያ ሥራዎችን ማከናወን፣

ተግባር 2፡- የፕሮግራም በጀት ዝግጅትና ትግበራ ለማገዝ የሚያስችል የፕሮግራም ዓላማዎች፣ ውጤቶች፣ የውጤት አመላካቾች እና ግቦች እንዲሁም የፕሮጀክቶች ዝርዝር መረጃ (Project Profile) እና አፈፃፀም የሚያሳይ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ ማዘጋጀትና መተግበር፣

ተግባር 3፡- የመሰረታዊ አገልግሎት የፕሮግራም ዓላማዎች፣ ቁልፍ ውጤት አመልካቾች፣ የውጤት ዕቅድ፣ግብና አፈጻጸም ዶክመንት ማዘጋጀት

ተግባር 4፡- ከዋና ዋና ባለበጀት መ/ቤቶች ጋር የውጤት ስምምነት (Performance Agreement) በመፈረም በፕሮግራም በጀት ውጤት አፈጻጸም ላይ ተጠያቂነት ማስፈን፣

ተግባር 5፡- የመንግስት ትልልቅ ፕሮጀክቶች አዋጭነት ጥናት ያላቸው እና በሚመለከታቸው አካላት የፀደቁ መሆናቸውን በማረጋገጥ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ፕሮጀክቶች በመለየት በበጀት እንዲካተቱ ማድረግ፣

ተግባር 6፡- የተሟላ ዓመታዊ የበጀት ዶክመንት ለማዘጋጀት በልዩ ሁኔታ የተቋቋሙ ፈንዶች በጀት በዓመታዊ የመንግስት በጀት ውስጥ ተቀፅላ በማድረግ ለመንግሥት ማቅረብ፣

ተግባር 7፡- ቅንጅታዊ አሰራር ማስፈን የሚያስቸል የክትትልና ግምገማ ስርዓት በመተግበር የፕሮግራሞችና የፕሮጀክቶች ውጤታማነትንና ወጪ ቆጣቢነትን ማረጋገጥ፣

ተግባር 8፡- የዕድገት እና የድህነት ተኮር ዘርፎችን የፕሮግራም የግብ ስኬቶችን፣ ውጤቶችን

እና የፕሮጀክቶችን አፈጻጸም በመገምገም አፈጻጸማቸውን ለመንግስት ማቅረብ፣

ተግባር 9፡- የፕሮግራም በጀት አሰራር ስርዓትን ወደ ክልሎች ማውረድ፣

ተግባር 10፡- በስራ ላይ ያለውን የፋይናንስ የጊዜ ሰሌዳ በጥናት ላይ በመመስረት ማስተካከያ ማድረግ፣

## የሚጠበቅ ውጤት

ውጤት 1፡- የተሻሻለ የፕሮግራም በጀት አሰራር ስርዓት አፈፃፀም፣

ውጤት 2፡- በመረጃ ስርዓት በመደገፍ የፕሮግራም እና የፕሮጀክት ፕሮፋይል መረጃ፣

ውጤት 3፡- በተሟላ ሁኔታ የተደራጀ የመሰረታዊ አገልግሎት የፕሮግራም ዶክመንት፣

ውጤት 4፡- ከመስሪያ ቤቶች ጋር የተፈረመ የውጤት ስምምነት (Performance Agreement) ዶክሜንት እና የሰፈነ ተጠያቂነት፣

ውጤት 5፡- በጥናት ላይ ተመስርተው ፋይናንስ የተደረጉ ፕሮጀክቶች፣

ውጤት 6፡- ልዩ ልዩ ፈንዶችን በዓመታዊ መንግስት በጀት ውስጥ ያካተተ የበጀት ዶክመንት፣

ውጤት 7፡- የተዘረጋ የክትትልና ግምገማ ስርዓት እና የተረጋገጡ ውጤታማና ወጪ ቆጣቢ ፕሮግራሞች እና ፕሮጀክቶች፣

ውጤት 8፡- ለመንግስት የቀረበ የዕድገትና የድህነት ተኮር ዘርፎች የፕሮግራም የግብ ስኬት፣ ውጤትና ፕሮጀክቶች አፈጻጸም፣

ውጤት 9፡- ፕሮግራም በጀት ስርዓትን የተገበሩ ክልሎች፣

ውጤት 10፡- በጥናት ላይ ተመስርቶ የተስተካከለ የፋይናንስ የጊዜ ሰሌዳ፣

## ግብ-3 የመንግስት እዳና ክፍያዎችን ወቅታዊ፣ቀልጣፋና ወጪ ቆጣቢ ማድረግ፣

ተግባር 1፡- የነጠላ ትሬዠሪ ሂሣብ /TSA/ አጠቃቀም ላይ ጥናት አድርጎ ሥራ ላይ ማዋል፣

ተግባር 2፡- በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ፣በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ክፍያዎችን እና በፌደራል ባለበጀት መ/ቤቶች የሚደረጉ ወጪዎችን ቀጥታ በኤሌክትሮኒክ ስርዓት እንዲሆን ማድረግ፣

ተግባር 3፡- የመንግስት ጥሬ ገንዘብ ዕቅድ፣ የክፍያ መረጃና ማስረጃዎች ቅብብሎሽ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ማድረግ፣

ተግባር 4፡- የመንግስት ጥሬ ገንዘብ ጣሪያ አወሳሰንን በማሻሻል ለመስሪያ ቤቶች የሶስት ወር የጥሬ ገንዘብ ዕቅድና የክፍያ ጣሪያ መስጠት፣

ተግባር 5፡- የመንግሥት ሠራተኞች ዳታ ቤዝ ከIFMIS ፔይሮል ዳታ ቤዝ ጋር ማቀናጀት፣

ተግባር 6፡- የመንግስት ዋስትና ሂሳቦች በትክክል በመመዝገብ ወቅታዊ ማድረግ፣ በየወሩ ሂሳቡን ማስታረቅና በየሶስት ወሩ ዶክመንቶች ማዘጋጀት፣

ተግባር 7፡- የ2010-2014 የመካከለኛ ዘመን የብድር ስትራቴጂ በመቅረጽ መተግበር፣

ተግባር 8፡- የብድር የመረጃ ምዝገባ ስርዓትን(DMFAS) ወደ ተሻሻለ ስርዓት ማሳደግ፣

ተግባር 9፡- የብድር አስተዳደር የምዝገባ ስርዓት(DMFAS) ከIFMIS ጋር ማስተሳሰር፣

ተግባር 10፡- የአገር ውስጥና የውጪ ብድር አወሳሰድ ሥርዓት በማዕከል እንዲከናወን ማድረግ፣

## የሚጠበቅ ውጤት

ውጤት 1፡- የተተገበረ የነጠላ ትሬዠሪ ሂሣብ / Treasury Single Account/ ስርዓት፣

ውጤት 2፡- በኤሌክትሮኒክ ስርዓት ተቀናጅተው የተፈፀሙ ክፍያዎችና ወጪዎች፣

ውጤት 3፡- በወቅቱ የቀረቡ የጥሬ ገንዘብ ፍላጎቶች እና የክፍያ መረጃዎች፣

ውጤት 4፡- የተሻሻለ የጥሬ ገንዘብ ጣሪያ አወሳሰን ስርዓት፣

ውጤት 5፡- ከIFMIS ፔይሮል ዳታ ቤዝ ጋር የተቀናጀ የመንግሥት ሠራተኞች ዳታ ቤዝ፣

ውጤት 6፡- ወቅታዊ ሆኖ የተዘጋጀ የመንግስት ዋስትና ሂሳቦች ዶክሜንት፣

ውጤት 7፡- የተተገበረ የ2010-2014 የመካከለኛ ዘመን የብድር ስትራቴጂ፣

ውጤት 8፡- የተሻሻለ የብድር የመረጃ ምዝገባ ስርዓት፣

ውጤት 9፡- ከIFMIS ጋር የተሳሰረ የDMFAS ስርዓት፣

ውጤት 10፡- የተዘረጋ ማዕከላዊ የአገር ውስጥና የውጪ ብድር አወሳሰድ ስርዓት፣

## ግብ-4 የመንግስት ሂሳብ አያያዝና ሪፖርት አቀራረብ ደረጃን ማሻሻል፣

ተግባር 1፡- የመንግሥት ሂሣብ ሪፖርት ሙሉ በሙሉ የመንግሥት ሀብትና ዕዳ እንዲይዝ ለማድረግ ጥናት ማካሄድ፣

ተግባር 2፡- የሂሣብ አያያዝና የሪፖርት አቀራረብ ሥርዓቱ በሂደት ወደ ዓለም አቀፍ የፐብሊክ ሴክተር የሂሣብ አያያዝ ደረጃዎች /IPSAS/ እንዲሸጋገር ማድረግ፣

ተግባር 3፡- የመንግስት ሂሣብ ሪፖርት ቅብብሎሽ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ እንዲከናወን ማድረግ፣

ተግባር 4፡- በልዩ ሁኔታ የተቋቋሙ ፈንዶች ሂሳብ በዓመታዊ መንግስት ሂሳብ ውስጥ አጠቃሎ ማቅረብ፣

ተግባር 5፡- የመንግስት የሂሳብ ባለሙያዎች የሙያ ደረጃ ለማሻሻል የሰርተፍኬሽን ሥልጠና በመስጠት የሙያ ማረጋገጫ እንዲወስዱ ማድረግ፣

## የሚጠበቅ ውጤት

ውጤት 1፡- የመንግስት ሃብትና እዳን የያዘ ሂሳብ ሪፖርቱ፣

ውጤት 2፡- የተጠናና የተተገበረ የፐብሊክ ሴክተር የሂሣብ አያያዝ /IPSAS/ ስርዓት፣

ውጤት 3፡- በወቅቱ የቀረበ የሂሳብ ሪፖርት፣

ውጤት 4፡- ዓመታዊ የመንግስት ሂሳብ ሪፖርት ውስጥ የተካተቱ ልዩ ልዩ የፈንድ ሂሳቦች፣

ውጤት 5፡- የማስፈፀም አቅማቸው የተሻሻለ ሂሳብ ባለሙያዎች፣

## ግብ-5 የውስጥ ኦዲትና ቁጥጥር ሥርዓትን በማጠናከር ገንዘብ ሲያስገኝ የሚችለውን ፋይዳ ማረጋገጥ፣

ተግባር 1፡- በፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የኦዲት ኮሚቴ በማቋቋም የውስጥ ቁጥጥር ስርዓቱን ማጠናከር፣

ተግባር 2፡- የውስጥ ኦዲት የሙያ ደረጃ በማዘጋጀት የኦዲት ሪፖርት ጥራትን ማሻሻል፣

ተግባር 3፡- የውስጥ ኦዲተሮችን የማስፈፀም አቅም ለማሻሻል የሰርተፊኬሽን ስልጠና (CIA) በመስጠት የሙያ ማረጋገጫ እንዲወስዱ ማድረግ፣

ተግባር 4፦ የክዋኔ ኦዲትን የመንግስት መስሪያ ቤቶች በማካሄድ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ፋይዳ ማረጋገጥ፣

ተግባር 5፦ የኦዲት ሥራዎች በመረጃ ስርዓት እንዲደገፉ ማድረግ፣

ተግባር 6፦ ሥጋትን መሰረት ያደረገ የኦዲት አሰራር በመተግበር የውስጥ ቁጥጥር ስርዓቱን ማጠናከር፣

ተግባር 7፦ የኦዲት ክትትልና ግምገማ ስርዓትን ማጠናከር፣

## የሚጠበቅ ውጤት

ውጤት 1፦ የተጠናከረ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት፣

ውጤት 2፦ በጥራት የተዘጋጀ የውስጥ ኦዲት ሪፖርት፣

ውጤት 3፦ የማስፈፀም አቅማቸው የተሻሻለ የውስጥ ኦዲት ባለሙያዎች፣

ውጤት 4፦ የአጠቃቀም ውጤታማነቱ የተረጋገጠ የመንግስት ሃብት፣

ውጤት 5፦ የተቀላጠፈ የውስጥ ኦዲት አሰራር ስርዓት፣

ውጤት 6፦ የተጠናከረ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት፣

ውጤት 7፦ የተስተካከለ የኦዲት ግኝት እና የሰፈነ ተጠያቂነት፣

## ግብ-6 ዘመናዊ የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ሥርዓት መዘርጋት፣

ተግባር 1፦ የኤሌክትሮኒክ የመንግስት ግዥ(e-GP) ሥርዓት በመዘርጋት የመንግስት ግዥ አፈፃፀምን የበለጠ ግልፅ፣ቀልጣፋ፣ተደራሽ፣ከብልሹ አሰራር የፀዳና ተጠያቂነት የሰፈነበት እንዲሆን ማድረግ፣

ተግባር 2፦ የመንግስት ግዥ መረጃዎችን ለህዝብ ተደራሽ ማድረግ፣

ተግባር 3፦ የመንግስት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር መረጃ አያያዝና አጠቃቀምን ማሻሻል፣

ተግባር 4፡ የግዥ ኦዲት ክትትል ሥራን በቁልፍ የግዥ አፈፃፀም አመላካቾች(KPI)ላይ እንዲመሰረት ማድረግ፣

ተግባር 5፦ በመንግስት መ/ቤቶች ጥቅም ላይ የሚውሉ የንብረቶች ስታንዳርድን በማሳደግ ተግባራዊ የሚሆኑበት አሰራር መዘርጋት፣

ተግባር 6፡- የማዕቀፍ ግዥ አፈፃፀም ውጤታማነትን በመገምገም ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታውን ማሳደግ፣

ተግባር 7፡- የመንግስት ተሽከርካሪ ፍሊት ማኔጅመንት እና ትልልቅ የመገልገያ መሣሪያዎችን አስተዳደር፣አጠቃቀም እና ጥገናን በሚመለከት ውጤታማ የአሰራር ስርዓት መዘርጋት፣

ተግባር 8፡- የአገልግሎት ጊዜያቸውን የጨረሱ የመንግስት ንብረቶች ተመልሰው ሥራ ላይ የሚውሉበት ወይም የሚወገዱበትን ዘመናዊ የአሰራር ስርዓት መዘርጋት፣

ተግባር 9፡- የመንግስት የግዥና ንብረት አስተዳደር ባለሙያዎችን የማስፈፀም አቅም ለማሻሻል የፕሮፌሽነናል ሥልጠና መስጠት፣

## የሚጠበቅ ውጤት

ውጤት 1፡- በኤሌክትሮኒክ ዘዴ የተደገፈ የግዥ አሰራር፣

ውጤት 2፡- ለህዝብ ተደራሽ የሆኑ የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር መረጃዎች፣

ውጤት 3፡- ወቅታዊ የተደረጉ የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር መረጃዎች፣

ውጤት 4፡- ግልፅነትና ተጠያቂነት የሰፈነበት የግዥ አሰራር ስርዓት፣

ውጤት 5፡- በተመሳሳይ ደረጃ የተገዙ ወጥ የመንግስት ንብረቶች፣

ውጤት 6፡- ኢኮኖሚያዊ፣ቀልጣፋ እና ውጤታማ የማዕቀፍ ግዥ፣

ውጤት 7፡- የተዘረጋ ውጤታማ የመንግስት ንብረቶች አስተዳደር ስርዓት፣

ውጤት 8፡- የመንግስት ንብረት በማስወገድ የተገኘ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ፣

ውጤት 9፡- የማስፈፀም አቅማቸው የተሻሻለ የግዥና ንብረት አስተዳደር ባለሙያዎች፣

## ግብ-7 የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደርን በዘመናዊ የመረጃ ስርዓት መደገፍ፣

ተግባር 1፡- የተቀናጀ የፋይናንስ አስተዳደር መረጃ ሥርዓትን /IFMIS/ በሁሉም የፌዴራል ባለበጀት መሥሪያ ቤቶች ደረጃ በደረጃ መዘርጋትና ጥራቱን ማረጋገጥ ፣

ተግባር 2፡- ለባለበጀት መ/ቤቶች ባለሙያዎች በመረጃ ስርዓት አጠቃቀም ላይ ተግባራዊ ስልጠና መስጠት፣

ተግባር 3፡- የተቀናጀ የፋይናንስ አስተዳደር መረጃ ሥርዓትን ፕሮጀክት ጽ/ቤት አቅምን ማጠናከር፣

ተግባር 4፡- የተቀናጀ የፋይናንስ አስተዳደር መረጃ ሥርዓትን አግባብነት ካላቸው ሌሎች የመንግስት መረጃ ስርዓቶች ጋር ማቀናጀት፣

ተግባር 5፡- የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደሩን የሚደግፉ ሌሎች የመረጃ ስርዓቶችን በማልማት መተግበር፣

ተግባር 6፡- የመረጃ ማዕከል (Data Center) እና ሴኪዩሪ ደረጃ በማጠናከር አፈፃፀሙን ማሻሻል፣

ተግባር 7፡- የተቀናጀ የፋይናንስ አስተዳደር መረጃ ሥርዓትን በ5 ብሔራዊና ክልላዊ ቋንቋዎች እንዲሰራ ማስቻል፣

ተግባር 8፡- በወረዳ ኔት ያልተገናኙ አዳዲስ ወረዳዎች እና የክልል ቢሮዎችን ማገናኘት፣

ተግባር 9፡- የተጨማሪ ዲዛዝተር ሪከቨሪ ግንባታዎችን ማካሄድ፣

## የሚጠበቅ ውጤት

ውጤት 1፡- የተተገበረ የመንግሥት ፋይናንስ አስተዳደር የመረጃ ሥርዓት /IFMIS/፣

ውጤት 2፡- በመረጃ ስርዓቱ በአግባቡ መጠቀም የቻሉ ባለሙያዎች፣

ውጤት 3፡- የላቀ ውጤት ያስመዘገበ ፕሮጀክት ጽ/ቤት፣

ውጤት 4፡- የተቀላጠፈ የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር አሰራር፣

ውጤት 5፡- የተቀላጠፉ የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር አሰራሮች፣

ውጤት 6፡- መረጃ የመያዝ አቅሙ እና ደህንነቱ የተሻሻለ ስርዓት፣

ውጤት 7፡- በ5 ቋንቋ የለማ የተቀናጀ የፋይናንስ አስተዳደር መረጃ ሥርዓት ፣

ውጤት 8፡- በወረዳ ኔት መጠቀም የጀመሩ ወረዳዎች እና የክልል ቢሮዎች፣

ውጤት 9፡- የተገነባ ዲዛዝተር ሪከቨሪ፣

## ግብ-8 የመንግሥት ፋይናንስ አስተዳደሩ አሳታፊ፣ግልፅና ተጠያቂነት የሰፈነበት ማድረግ፣

ተግባር 1፡- በፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት እና የማህበራዊ ተጠያቂነት ስርዓትን መተግበር፣

ተግባር 2፡- በየደረጃው የሚገኙ የፌደራል እና ክልል መንግስት መ/ቤቶች የመንግስት ፋይናንስ መረጃዎችን አግባብነት ባላቸው የመገናኛ ብዙሃን አማካይነት ለዜጎች ይፋ ማድረግ፣

ተግባር 3፡- የመንግስት ልማት ድርጅቶች እና በልዩ ፈንድ የተቋቋሙ ድርጅቶች ዓመታዊ የኦዲት ሪፖርት ለሕዝብ ይፋ ማድረግ፣

ተግባር 4፡- በመንግስት የልማት ፕሮጀክቶች ላይ የዜጎች ተሳትፎን ማሳደግ፣

## የሚጠበቅ ውጤት

ውጤት 1፡- የተተገበሩ የፋይናንስ ግልፅነትና ተጠያቂነት እና ማህበራዊ ተጠያቂነት ስርዓት፣

ውጤት 2፡- ለዜጎች ይፋ የሆኑ የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር መረጃዎች፣

ውጤት 3፡- ለዜጎች ይፋ የሆኑ የመንግስት ልማት ድርጅቶች እና ልዩ ፈንድ የኦዲት ሪፖርቶች፣

ውጤት 4፡- በመንግስት የልማት ፕሮጀክቶች እቅድ እና አፈፃፀሞች ላይ የተሳተፉ ዜጎች፣

## ግብ-9 የመንግሥት ፋይናንስ አስተዳደር የማስፈፀም አቅምን ማጎልበት፣

ተግባር 1፡- የመንግስት ፋይናንስ፣ግዥና ንብረት አስተዳደር የህግ ማዕቀፎች፣ ማንዋሎች እና የስልጠና ሞጁሎች ወቅታዊ ማድረግ፣

ተግባር 2፡- በየመሥሪያ ቤቶች የመንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር ዘርፍ አደረጃጀት እንዲሻሻል በማድረግ በሰው ኃይል ማደራጀት፣

ተግባር 3፡- የመንግሥት ፋይናንስ አስተዳደርን ለማጠናከር የለውጥ መሣሪያዎችን መተግበር፣

ተግባር 4፡- የበላይ እና የመካከለኛ አመራሮች የመንግሥት ፋይናንስ አስተዳደር የአመራር ብቃታቸውን በማጎልበት ኃላፊነትና ተጠያቂነትን ማስፈን፣

ተግባር 5፡- ለመንግሥት መ/ቤቶች ባለሙያዎች በመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር ላይ ተቋማዊ ሥልጠና በመስጠት የማስፈፀም አቅማቸውን ማጎልበት፣

ተግባር 6፡- የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር አሰራር በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ስርዓተ ትምህርት ውስጥ ተካቶ በመደበኛነት ትምህርት እንዲሰጥበት ማድረግ፣

ተግባር 7፡- በአገር ውስጥ ባሉ የትምህርትና ስልጠና ተቋማት የተመሰከረላቸው የሂሳብ አዋቂዎች እና የኦዲት ስልጠና እንዲሰጥ ማድረግ፣

### የሚጠበቅ ውጤት

ውጤት 1፡- የተጠናከረ ጥብቅ የህግ ዲሲፕሊን፣

ውጤት 2፡- የተጠናከረ የማስፈፀም አቅም፣

ውጤት 3፡- የተሻሻሉ የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርዶች፣

ውጤት 4፡- በጥብቅ ዲሲፕሊን የሚመራ የመንግስት ፋይናንስ አሰራር ስርዓት፣

ውጤት 5፡- የማስፈፀም አቅማቸው የተሻሻለ ባለሙያዎች፣

ውጤት 6፡- በመንግሥት ፋይናንስ አስተዳደር ላይ በቂ እውቀት ያገኙ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች፣

ውጤት 7፡- በሂሳብ አያያዝ እና ኦዲት የማስፈፀም አቅማቸው የተሻሻሉ ባለሙያዎች፣

# 7. የስትራቴጅው አመራርና ተቋማዊ አደረጃጀት

## 7.1. ስትራቴጅውን ለመምራት ዋና ዋና መሰረታዊ ጉዳዮች (Main Principles)

- ስትራቴጅውን ለመምራት በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ስር የራሱ የሆነ መዋቅራዊ አደረጃጀት ያለው የማሻሻያ ፕሮግራም ማስተባበሪ ጽ/ቤት ይኖረዋል፣
- አደረጃጀቱም ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በሚሰጠው አመራር ተዘጋጅቶ በሚፀድቅ ዕቅድ መሰረት እንዲሁም ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ስትራቴጅውን ይመራል፣

- የተቋቋመው ክፍል በቴክኒክ ኮሚቴ እና እንደአስፈላጊነቱም በአማካሪዎች የሚደገፍና የሚሰራ ይሆናል፣
- የተቋቋመው ክፍል የቴክኒክ ኮሚቴውንና የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት የማስተባበርና ውጤቱ እንዲገኝ ኃላፊነት አለበት፣
- ስትራቴጂው በቀጥታ በከፍተኛ አመራሩ የሚመራ ክትትልና ግምገማ የሚደረግበት ይሆናል፣

## 7.2. ተቋማዊ አደረጃጀት፣ ክትትልና ግምገማ

### 7.2.1. ተቋማዊ አደረጃጀት

በስትራቴጅው ውስጥ የተቀመጡትን ግቦች ለመተግበር እና ዓላማዎችን ለማስፈፀም አግባብነት ያለው ተቋማዊ አደረጃጀትና የትግበራ ክትትል ያስፈልጋል፡፡ ስትራቴጅውን ለማስፈፀም አገር አቀፍ አመራር፣ PFM streeing Committee፣የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር ቡድን ፣ ልዩ ልዩ የቴክኒክ ኮሚቴዎች እና ስትራቴጅውን በዋናነት የሚያቅድና የሚያስፈጽም ጽህፈት ቤት ይኖሩታል፡፡ እነዚህም በዝርዝር ሲታይ፡-

ሀ) በአገራቀፍ ደረጃ የማሻሻያ ፕሮግራሙን በበላይነት የሚመራ የመንግስት ከፍተኛ አመራር አካላትን የያዘ አገር አቀፍ አመራር (National Steering Committee) ፣

ለ) የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር የበላይ አመራርና የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር ቡድን አባላት እንዲሁም የክልል ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ኃላፊዎች የሚገኙበት ኮሚቴ (PFM Steering Committee) ፣

ሐ) የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር የስትራቴጂውን ትግበራ የሚያስፈጽም ዳይሬክቶሬት፣ የፕሮጀክት ቴክኒክ ኮሚቴ ሰብሳቢዎች፣ የቻናል አንድ ፕሮግራሞች ማስተባበሪያ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር፣ የህዝብ ግንኙነት የኢንፎርሜሽን ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር፣ የህግ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር እና የፊስካል ፖሊሲ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር የሚገኙበት የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር ቡድን (PFM team) ፣

መ) በክልል/ከተማ አስተዳደር የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮዎች በቢሮ ኃላፊው የሚመራና ሆኖ የፋይናንስ ዘርፍን የሚመራዉ ምክትል ቢሮ ኃላፊና የሚመለከታቸው ስራ ክፍሎች፣ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ኃላፊዎች የሚገኙበት የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር ቡድን (PFM team) ፣

ተቋቁመው ሥራውን በየደረጃው ይመሩታል፡፡

## 7.2.2. ክትትልና ግምገማ

የክትትልና ግምገማ ሥራዎችም በተመለከተ፡-

- አገር አቀፍ አመራር (National Steering Committee) በየስድስት ወሩ፣
- የሚኒስቴሩ የበላይ አመራር፣ የሚመለከታቸው ዳይሬክቶሬቶች እና የክልል/ከተማ አስተዳደር ገ/ኢ/ት/ ቢሮ ኃላፊዎች የሚገኙ የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር ቡድን (PFM Steering Committee) የምክክር መድረክ በዓመት ሁለት ጊዜ፣
- በሚኒስቴሩ የበጀትና ክፍያዎች ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ የሚመራ የሚመለከታቸው ዳይሬክቶሬቶች የሚሳተፉበት በወር አንድ ጊዜ፣
- በሚኒስቴሩ የተደራጁት የየፕሮጀክቱ ቴክኒክ ኮሚቴዎች በየሳምንቱ አንድ ጊዜ፣
- በማስተባበሪ ዳይሬክቶርቱ ደረጃ ፕሮጀክቶችን የሚያስተባበሩ በየሳምንቱ አንድ ጊዜ እንዲሁም በመደበኛነት በየስድስት ወሩ ከክልሎች ጋር፣

በመገናኘት የስትራቴጀውን ዕቅድ አፈጻጸምና የሥራ ሂደት ይገመግማሉ፤ ቀጣይ አቅጣጫንም ያስቀምጣሉ።

የየፕሮጀክቱ ቴክኒክ ኮሚቴዎች ከሚኒስቴሩ እና ከመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የተውጣጡ አባላት ይኖሩታል፡፡ እያንዳንዱ የቴክኒክ ኮሚቴ ከአራት እስከ ስድስት አባላት ያሉት ሲሆን ዝርዝራቸውም የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. የፕሮግራም በጀት ቴክኒክ ኮሚቴ፣
